# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 83ኛ ዓመት ቁጥር 247 ግንቦት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# "ብልጽግና የየትኛውም ብሔር የዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት አለባቸው ብሎ ያምናል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የየትኛውም ብሔር የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች በተገቢው መልኩ ምላሽ ማግኘት አለባቸው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ ሀገሪቱ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ያልተቋራረጠ ዕድገት ማስመዝገቧን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰሞኑን በጎርጎራ በተካሄደው የብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባላት የዘጠኝ ወር የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ገለጻ ሰጥተዋል፡፡

የፓርቲው ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ፤ የብሔር ጥያቄ ላለፉት 50ና 60 ዓመታት ዋነኛ የፖለቲካ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እንደነበር አንስተዋል፡፡

የራስን ብሔር፣ ቋንቋ፣ ባህል መሠረት ያደረጉ ንግግሮችና ክርክሮችም ሰፊ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እኛ እንደብልጽግና የየትኛውም ብሔር የሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች በተገቢው መልኩ ምላሽ ማግኘት እንዳለባቸው እናምናለን ብለዋል፡፡

የብሔሮች መብትና ጥያቄ ምላሽ አግኝቶ በሀገር ጥላ ስር ካልተሰባሰብን በስተቀር ለአንድ ብሔር ብቻ በመታገል ሀገር መገንባት አይቻልም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

"ብልጽግና የየትኛውም ብሔር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ሀዲስ አብርሃ

## "ባለሥልጣኑ የዓለም የቅርስ ምርምር ልህቀት ማዕከል ለመሆን መሥራት ይገባዋል››

- አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የቱሪዝም ሚኒስትር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን በዓለም አቀፍ ደረጃ የቅርስ ምርምር ልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችል ሥራ ማከናወን እንዳለበት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ አሳሰቡ። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ዓመታዊ የቅርስ

"ባለሥልጣኑ የዓለም ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



ጻድቁ አብዶ (ፓስተር)

## ምክክሩ

### ለሀገሪቱ ችግሮች መፍትሄ በመሆኑ ሁሉም ሊደግፈው ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ ሀገሪቱ ላሉባት ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ የሚያበጅ በመሆኑ ሁሉም ሊደግፈውና ሊሳተፍ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ

ምክክሩ ለሀገሪቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የመካከለኛው ምስራቅ ወላፈን በምስራቅ አፍሪካ የሚኖረው አንድምታ?

**ልጅዓለም ፍቅሬ**


አንዳንድ የፖለቲካ ምሁራን እንደሚገልጹት ዓለም የባላንጣዎች እኩይ ሴራ መፈጸሚያ መሆኗ እያደር እየገዘፈ መጥቷል። በዚህም የተነሳ በርካታ ዜጎች ሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ተነፍገው የለቅሶና የዋይታ ሲቃ ማሰማት ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

የሃማሱ ታጣቂ ቡድን በእስራኤል ግዛቶች ሰርጎ በመግባት ጥቃት ካደረሰ ወዲህ በመካከለኛው ምስራቅ ቀጣና የማያባራ የበቀል ዶፍ እየወረደ ይገኛል። ጦርነቱ ከጀመረም ስድስት ወራት አልፏል።

በዚህም ጦርነት በርካታ ንጹሃን ዜጎች ለከፋ ጉዳት ከመዳረግ አልፎ ውድ የሆነ ሕይወታቸውን ገብረዋል። ታዲያ ጦርነቱ በቀጣናው ተጀምሮ የሚቋጭ ሳይሆን ዳፋው ለመላው ዓለም የሚተርፍና የዓለማችን ባለፈርጣማ ክንድ ሀገራት በሁለት ጎራ የሚከፍልም ይመስላል። እስካሁን በሚታዩ መነቋቆሮችና ትንኮሳዎች ጦርነቱ ወደ ሌሎች ቀጣናዎች ይዛመታል የሚለው መላምት ሳይታለም የተፈታ ነው።

በመካከለኛው ምስራቅ እየተቀጣጠለ ያለው ወላፈን ለዘመናት በመልካም አስተዳደርና ቅጥ ባጣ

የመካከለኛው ምስራቅ ወላፈን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል






# ብዝሃነትን ያገናዘበ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ረቂቅ አዋጅ

## ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመራ

### - ሰዎች ብሄራቸው ብቻ ታይቶ ሥራ ወይንም ሹመት ሊሰጣቸው አይገባም ተብሏል

**ዘሳስም ግዛው**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብዝሃነት እና አካታችነትን ያገናዘበ ኢትዮጵያን የሚመስል የመንግሥት ሠራተኞች ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መራ።

ሰዎች ብሄራቸው ብቻ ታይቶ ሥራ ወይንም ሹመት ሊሰጣቸው እንደማይገባ ከምክር ቤት አባል ተጠቁሟል።

አዋጁ በምክር ቤቱ የቀረበው ትናንት በተካሄደው ሶስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን 26ኛ መደበኛ ስብሰባ ነው።

የአዋጁን ማብራሪያ ለምክር ቤቱ ያቀረቡት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ እንደገለጹት፤ ብሄራዊነት የአካል ጉዳተኞች፣ የጾታ ተዋጽኦና የመሳሰሉትን ብዝሃነትና አካታችነትን ያገናዘበ የመንግሥት ሠራተኞችን ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ የመንግሥት አስተዳደርና ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቁ ተዘጋጅቷል።



የመንግሥት ሠራተኞች የሰው ሃይል ምልመላና መረጣ ግልጽነት ባለው ውድድርና ብቃት ላይ የተመሠረተ ሆኖ የደመወዝ ጭማሪ፣ የደመወዝ እርከን ክፍያና ጥቅማ ጥቅም፣ ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል ብለዋል።

የመንግሥትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበት የዜጎችን ፍላጎት የሚያረካ የመንግሥት አገልግሎት እና አስተዳደር ሥራ ለመስጠት የሚያስችሉ የሕግ ድንጋጌዎች ተካትተው የቀረቡበት ረቂቅ አዋጁ፤ በ17 ክፍሎች እና በ 160 አንቀጾች የተዋቀረ ነው።

አዋጁን ማሻሻል ያስፈለገው የመንግሥት ሠራተኞች የሰው ኃይል ምልመላና መረጣ ግልጽነት ባለው ውድድርና ብቃት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሥራን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት በማለም ነው ብለዋል አቶ ተስፋዬ።

በረቂቅ አዋጁ ማሻሻያ ተደርገው ከቀረቡ ዓበይት ጉዳዮች፤ የደመወዝ ጭማሪ፣ የደመወዝ እርከን ክፍያና ጥቅማ ጥቅም፣ ማትጊያ ወይንም ማበረታቻ ሥርዓት፣ የሠራተኞች ብቃት መመዘኛና ማረጋገጫ፣ ሥልጠና አሰጣጥ፣ ሥራ ስምሪት እና ነጻ ገለልተኛ ሥርዓት መገንባትን የሚመለከቱ ይጠቀሳሉ።

እንዲሁም ብዝሃነት፣ አካታችነት እና ተጨማሪ የድጋፍ ርምጃ አፈጻጸም የመንግሥት ሠራተኛነት የሥራ ውል ማቋረጥ እና ማራዘም፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ምርመራ ሥራ አገልግሎት አቅርቦትና ደረጃን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል።

የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 በሥራ ላይ ከዋለ የስድስት ዓመታት እድሜን ያስቆጠረ በመሆኑ በአዲስ የመንግሥት አገልግሎት አስተዳደርና አገልግሎት ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ጋር ማጣጣም ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል።

ነባሩ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በትግበራ የታዩ ችግሮችን በመፍታት የመንግሥትን የመፈጸም ብቃት ማጎልበት፣ የዜጎችን አገልግሎት የሚያረካ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ጠቅሰዋል።

የምክር ቤት አባላት ካለው የኑሮ ውድነት አኳያ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም እና ማትጊያ ሥርዓት እንዲዘረጋ መደረጉ በጣም ጥሩ መሆኑን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የጾታ ተዋጽኦና የመሳሰሉትን ብዝሃነትና አካታችነትን ያገናዘበ ሆኖ መቅረቡን በበጎነት አንስተዋል።

«ነገር ግን ብሄር ብሄረሰብን እናስተናግዳለን ስንል ጥንካሬና ብቃታቸውን በማየትና በማገናዘብ ሊሆን ይገባል እንጂ፤ ሰዎች ብሄራቸው ብቻ ታይቶ ሥራ ወይንም ሹመት ሊሰጣቸው አይገባም» የሚል አስተያየት አንድ የምክር ቤት አባል አቅርበዋል።

ለብቃት ልዩ ቦታ መስጠት ይገባል ያሉት የምክር ቤት አባሉ፤ እንደ ሀገር ማሰብ ይገባል እንጂ ለብሄራችን ማሰብ የለብንም። አንድ ሰው አቅሙ እያለው በብሄሩ ምክንያት ከደረጃ ዝቅ እንዳይል ወይም ከሥራው እንዳይፈናቀል መሥራት ይገባናል፤ ቋሚ ኮሚቴው ረቂቅ ሕጉን ሲያየው እነዚህን ጉዳዮች ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ምክር ቤቱ በትናት ውሎው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅን፣ የሜዳይ፣ ኒሻንና ሽልማት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

የኢትዮጵያ ደረጃዎች ረቂቅ አዋጅን፣ የሁለት ዳኞች የሥራ ስንብትን፣ የሕጋዊ ሥነልክረቂቅ አዋጅንና የተጨማሪ እሴት ታክስ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል።



ተከተል ዮሃንስ (ፕ/ር)

# ለጽዱ ኢትዮጵያ

## የተጀመረው እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት አሳይቷል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ለጽዱ ኢትዮጵያ የተጀመረው እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት እየታየበት እንደሆነና ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ሥራ አስፈጻሚ ተከተል ዮሃንስ (ፕ/ር) የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄን አስመልክተው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሥራዎች የተጀመሩት እንደ ሀገር ዘግይተው ቢሆንም በአጭር ጊዜ አበረታች ተሳትፎ እየታየ ነው። በመሆኑም ይህንን አጠናክሮ በመቀጠል እንደ አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ለውጥ ማስመዝገብ ይጠበቃል።

በአዲስ አበባ የተጀመረው ሥራ ሳይቀዛቀዝ በተጓዳኝ በሌሎች ከተሞችም ሊካሄድ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር ተከተል፤ ለዚህ ደግሞ የተጀመሩ ማህበረሰቡንና ባለሀብቶችን የማሳተፍ እንቅስቃሴ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብለዋል።

ከዛሬ ሰላሳ ዓመት በፊት እንደዚህ አይነት ሥራዎችን በሠለጠኑት ሀገራት ስንመለከት ምነው በሀገራችን በተሥሩ ስንል ነበር። ከሌላው ዓለም አንጻር የዘገየንና ኋላ የቀረን ቢሆንም አሁንም መጀመሩ ግን ይበል የሚያሰኝ ነው። በመሆኑም እንደ ሀገር ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል ሲሉም አጽኦት ሰጥተዋል።

በተለይም እንደ ማህበረሰብ በየመንገድ ዳርቻ የሚሠሩ መጸዳጃ ቤቶች ምንም እንኳን ደረጃቸውን ጠብቀው የሚገነቡ ቢሆንም ማህበረሰቡ በአግባቡ ካልተጠቀመባቸው የሚጠበቀው ውጤት ሊገኝ አይችልም ያሉት ፕሮፌሰር ተከተል፤ በመሆኑም መሠረተ ልማት ከማሟላት በተጓዳኝ የአመለካከት ለውጥ እንዲፈጠርም በርካታ ሥራዎች ይጠበቅብናል። ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ ከቻልን እንደ ሀብት ለመጠቀም እድሉ ይኖረናል። በዚህ ረገድ እንደ ማህበረሰብ ያለን አመለካከት እንዲቀየርም በርካታ ሥራ ይጠይቃል ብለዋል።

ፕሮፌሰር ተከተል እንደገለጹት፤ በጽዱ ኢትዮጵያ ተግባራዊ መሆን የማይጠቀም ዜጋ አይኖርም። ይህም ጉዳዩ ብሄራዊ አጀንዳችን መሆኑን ያመላክታል። እኛ በሀገር ውስጥ ከምናገኘው ጠቀሜታ ባለፈ የውጭው ዓለም ሕዝብ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ያለውን አመለካከት እንዲያስተካክል የሚረዳው ይሆናል። በመሆኑም ጉዳዩን የመንግሥት ወይንም የአንድ አካል ከማድረግ ተላቀን ሁላችንም አቅማችን በፈቀደ የተጀመረውን ዘመቻ ልንተባበር ይገባል።

# የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም ባህል ማድረግ ያስፈልጋል

### - በኤክስፖው ሰባት የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያን ምርት ለመግዛት ተስማምተዋል

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ዘላቂ የገበያ ትስስር የመፍጠርና የሀገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ባህልን ማሳደግ የሁሉም የቤት ሥራ ሊሆን እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ተናገሩ።

በኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ሰባት የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያን ምርት ለመግዛት መስማማታቸው፣ ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት መከናወኑና 74 የመንግሥት ተቋማት አብሮ የመሥራት ትብብር መፍጠራቸው ተመላክቷል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ማጠቃለያ መርሐግብር ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የአምራች ኢንዱስትሪውን የሀገር ውስጥ ገበያ ድርሻ ማሳደግ የሚያስችለውን የተኪ ምርት ስትራቴጂ በመተግበር የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ይገባል።

መንግሥት ለዘርፉ ዕድገት ልዩ ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ እንድታመርት ብቻ ሳይሆን ያመረተችውን እንድትጠቀምም ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል ያሉት አቶ ተመስገን፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የሀገር ውስጥ ምርትን የመጠቀም ባህሉ ሊያሳደግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት መቀነስና የሀገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ባህልን ማሳደግ የግድ ይላል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታትና የተኪ ምርቶችን ስብጥር ለማሳደግ የመንግሥት ተቋማት የሀገር ውስጥ ምርትን እንዲገዙ የተቀመጠውን አቅጣጫ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።



ፎቶ ገብዩ ገብሬ

ተመስገን ጥሩነህ

ኢትዮጵያ ካላት የልማት ፍላጎትና የመልማት አቅም እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪው ካለበት ዘርፈ ብዙ ማነቆዎች አኳያ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ እንደሚያስፈልግ አመላክተው፤ በዚህም የኢትዮጵያ ታምርት ንቅንቄ ሊያሳካ የያዛቸውን ግቦች መተግበር እና የአምራች ኢንዱስትሪውን ማነቆ በመፍታት ውጤት ማምጣት ይገባል ብለዋል።

የፋይናንስና የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሳደግ፣ በጥራትና በብዛት በማምረት፣ የገበያ አማራጮችን እና የገበያ ትስስሮችን በማስፋፋት ተወዳዳሪ መሆን እንደሚገባ ተናግረዋል።

በኤክስፖው የዘርፉን ማነቆ ለመፍታት አማራጭ መፍትሄዎች እና የኢትዮጵያን ምርት በማስተዋወቅ ዘላቂ የገበያ ትስስር መፈጠሩን አንስተው፤ እንደሀገር ያሉንን የልማት እድሎች የመጠቀም እና የአምራች ኢንዱስትሪውን ማነቆ በቅንጅት መፍታት የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ዓላማ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከግንቦት 1 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ግንቦት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ሲካሄድ በቆየው የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከ210 በላይ ኩባንያዎች ምርታቸውን አቅርበው ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ተከናውኗል።

74 የመንግሥት ተቋማት አብሮ የመሥራት ትብብር መፍጠራቸውና ሰባት የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያን ምርት ለመግዛት መስማማታቸውን አስረድተዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፣ በኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከ100 ሺህ በላይ ግለሰቦችና ተቋማት ተሳትፈዋል። ከ57 ሀገሮች የመጡ ድርጅቶች እና 157 ዲፕሎማቶች አስተዋጽኦ አበርክተዋል ብለዋል።

በኤክስፖው 210 አምራች ኢንዱስትሪዎች መሳተፋቸውን ገልጸው፤ አምስት ሺህ 188 የአይነት ግብይት እና ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ በገንዘብ ደረጃ ግብይት መከናወኑን ተናግረዋል።

በኤክስፖው የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግር የሚፈታና በፖሊሲ የሚደግፍ አራት የፓናል ውይይት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት መካሄዱን ገልጸው፤ በፓናል ውይይቱም ከ837 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የ2017 ኤክስፖ ከሚያዚያ 30 እስከ ግንቦት 6 ቀን 2017 ዓ.ም ለሰባት ቀን እንዲካሄድ መወሰኑንም ጠቁመዋል።



ፎቶ፡- በረሁን ታደሰ

## “የዞኑ ሕዝብ ለልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በባለቤትነት እየሠራ ነው”

**- አቶ ሀብታሙ ካፍትን የቤንች ሸኮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ**

**ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

ሚዛን አማን፡- የዞኑ ሕዝብ ለልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በባለቤትነት እየሠራ መሆኑን የቤንች ሸኮ ዞን አስተዳደር አስታወቀ።

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሀብታሙ ካፍትን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በዞኑ በተፈጠረው ሰላም ባለሀብቱና አርሶ አደሩ ሙሉ ትኩረቱ ልማት ላይ ይገኛል።

ሸኮ ቤንች ላይ ማህበረሰቡ በራሱ ወጪ የ28 ሚሊዮን ብር ድልድይ እየገነባ መሆኑን አንስተው፤ ሸኮ ላይ በ22 ሚሊዮን ብር፣ ደቡብ ቤንች ላይ ደግሞ በ28 ሚሊዮን ብር ጤና ጣቢያ እየገነባ መሆኑን አስታውቀዋል።

ለስፖርቱ ዘርፍም በተሰጠው ትኩረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስታዲየም በ80 ሚሊዮን ብር ግንባታ እያካሄደ ነው ብለዋል።

ህብረተሰቡ ለልማቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑንና አርሶ አደሩ ቡና በኪሎ እንዲያወጣ በማድረግ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ሸኮ ላይ 30 ሚሊዮን ተሰብስቧል ሲሉ ተናግረዋል።

ልማቱን ለማፋጠን በተለይ ከአውሮፕላን ማረፊያ ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስተዳደሩ ውይይት እያደረገ በትብብር እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ዞኑ ለአውሮፕላን ማረፊያ ልማቱ ከፍተኛ ፍላጎት ስላለው ትኩረት ሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት ዋና አስተዳዳሪው፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመሠረተ ድንጋይ ከተመቀጠ ጀምሮ ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን ግንባታው 62 በመቶ ደርሷል ብለዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ ከሆነ፤ በዞኑ ከፍተኛ የቱሪዝም እምቅ ሀብት አለ። ደንቢ ሃይቅ ፣ በበቃ ፣ ሸካ እና ደቡብ ቤንች ያሉ አካባቢዎች በተፈጥሮ ምንም ሳይነካ እና ሳይበረዝ ያለ ድንቅ የቱሪዝም አካባቢ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በልዩነት ‹‹የደንቢን ሎጅ›› ፕሮጀክት ያስጀመሩት ዞኑ ባለው የቱሪዝም ሀብት በመደነቃቸው ነው ብለዋል። ይሁንና አሁንም ዞኑ ካለው እምቅ ሀብት አንጻር የቱሪዝም ቦታዎችን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ክፍተት እንዳለ አመላክተዋል።

በተጨማሪም በገበታ ለትውልድ የሚሠራው ‹‹ደንቢ ሎጅ›› ከተጠናቀቀ ቀጣናው ከፍተኛ የቱሪዝምና የኢኮኖሚ የስበት ማዕከል ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል።

አሁን ላይ ዞኑ አቅሙ የሚፈቅደውን ሁሉ እየሠራ መሆኑን ተናግረው፤ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ የሚመለከታቸው አካላት፤ በተለይም የገንዘብ ሚኒስቴር ፕላን ሚኒስቴር ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ጠይቀዋል።

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከአቶ ሀብታሙ ካፍትን ጋር ያደረግነው ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ አምዳችን ላይ ያገኙታል።

# የወሎ ሰፈር ሚኒ ሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት

## በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ድጋፍ ያደርጋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የወሎ ሰፈር ሚኒ ሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ መከላከያ ለከንዓን ግሩፕ ያልተቆጠበ ድጋፍ ያደርጋል ሲሉ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ ገለጹ።

በመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ይዞታ ስር በነበረው ወሎ ሰፈር ለሚገነባው ከነዓን ታውን ሺፕ የሚኒ ሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት የመሠረት ድንጋይ ተጣለ።

በዚሁ ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙት የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ እንዳሉት ፤ ለረጅም ዓመታት በመከላከያ ይዞታ ስር የነበሩ መሬቶች መልማት በሚገባቸው ልክ ሳይለሙ ቆይተዋል።

አሁን ላይ ተቋሙ ከሚያከናውነው የለውጥ ሥራ አኳያ በርካታ አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ጀምረናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የወሎ ሰፈር ሚኒ ሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ መከላከያ ለከንዓን ግሩፕ ያልተቆጠበ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል። መከላከያ የጀመረውን መጨረስ የሚችል ያሰበውንም የሚያሳካ ተቋም መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ሰለሞን ደመቀ፣ ኢንተርፕራይዙ በአቅሙ ልክ ሚናውን መጫወት እንዳይችል ያደረጉት በርካታ ማነቆዎች አሁን ላይ የተፈቱ መሆናቸውን ጠቁመው፤ አቅሙን ከፍ የሚያደርጉ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

የወሎ ሰፈር ሚኒ ሲቲ ግንባታ የበርካታ ዲፕሎማት መቀመጫ ለሆነችው የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የከንዓን ታውን ሺፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በረከት ጎይቶም ገልጸዋል።

ባለ 24 ወለል ዘመናዊ የመኖሪያ አፓርታማዎች፣ የንግድ ደረጃቸውን የጠበቁ ሞሎች ለዕይታ ማራኪና ዘመናዊ መንገዶች፣ የቢሮ ህንጻዎች፣ ለከተማ መለያ የሚሆን የተዋበ የአርክቴክት ውጤትን ያካተተው የሚኒ ሲቲ ግንባታው ለዘመናዊ ከተማነት ጉልህ ድርሻ የሚያበረክቱ መሆናቸውን መናገራቸውን ከኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# የትምህርት ተቋማትና የአምራቾችን ትስስር ፈር በማስያዝ

## ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መገንባት ያስፈልጋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ተቋማትና አምራቾችን ትስስር ፈር በማስያዝ ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መገንባት ያስፈልጋል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) ገለጹ፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ 1298/2015ን ተከትሎ ብሔራዊ የትስስር ምክር ቤት አደረጃጀትና አባላት ምስረታ መድረክ ትናትና ተካሂዷል፡፡

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በመድረኩ እንደገለጹት፤ የኢንዱስትሪ ዘርፉን በሚፈለገው ልክ ለማሳደግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የትስስር ቁልፍ ሥራዎችን በተሻለና በተቀናጀ መንገድ በመተግበር ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መገንባት ይኖርባቸዋል።



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)

የብሔራዊ ትስስር ምክር ቤት መቋቋም የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሻሻል፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለማሳደግ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይል ክፍተትን ለማስቀረት፣ የተግባር ሥራዎችን ለማሳየትና ሀገራዊ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚያግዝም ተናግረዋል።

ሥራ ፈጠራ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ አቅምን ማሳደግ፣ ከኢንዱስትሪ ወደ አካዳሚና ከአካዳሚክ ወደ ኢንዱስትሪ ትስስር ማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር አገልግሎት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ትስስሩን ለማጠናከር ያለው የቁርጠኝነት ማነስ፣ ሥራውን እንደ ተጨማሪ ተግባር መመልከት፣ ክትትልና ርምጃው ደካማ መሆንና መሰል ችግሮች ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ተግዳሮቶቹን በተቀናጀና በጥናት ላይ በተመሠረቱ ሥራዎች መፍታት ያስፈልጋል ብለዋል።

በተጨማሪም የትስስር ሥራን በተገቢው መንገድ ለማስፈጸም የሚረዳ አስገዳጅ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር ተግዳሮት መሆኑ ገልጸው፤ በቀጣይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የትምህርት ተቋማትና ኢንዱስትሪዎችን ትስስር አስገዳጅ የሚያደርግ ሕግ እንዲወጣ ጥረት ይደረጋል ሲሉ አመላክተዋል።

በቀጣይ ኢንዱስትሪውን በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ ተቋማት በቴክኖሎጂ የታገዙና ችግር ፈቺ የምርምር ሥራዎች ላይ በኃላፊነት ስሜት ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅን ወደ ሥራ ለማስገባት ስድስት መመሪያዎች መዘጋጀታቸውም በመድረኩ ተገልጿል፡፡

በመድረኩ ከትምህርት ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) በተጨማሪ የተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## “ኤክስፖው የቴክኖሎጂው ዘርፍ ሥራዎችን የሚያስተዋውቅና የገንዛቤ እጥረቶች የሚቀርፍ ነው”

**- ይሽሩን አለማየሁ(ዶ/ር) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ትኩረቱን በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ላይ አድርጎ የሚካሄደው “ስትራይድ ኢትዮጵያ” ኤክስፖ በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የሚያስተዋውቅና የሚታዩ የግንዛቤ እጥረቶች የሚቀርፍ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ(ዶ/ር) ገለጹ።

ኤክስፖው “ሳይንስ በር ይከፍታል፣ ቴክኖሎጂ ያስተሳስራል፣ ፈጠራ ወደፊት ያራምዳል” በሚል መሪ ሃሳብ ከግንቦት 10 እስከ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ይካሄዳል።

ኤክስፖውን በማስመልከት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ(ዶ/ር) መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንዳስታወቁት፤ ኤክስፖው በቴክኖሎጂው ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የሚያስተዋውቅና የሚታዩ የግንዛቤ እጥረቶች የሚቀርፍ ነው።

በተጨማሪም በአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከርና በዘርፉ የተጀመሩ ጠንካራ ልምዶችን ለማጠናከር እንዲሁም ትብብር ለመፍጠር ያለመ መሆኑን ተናግረዋል።

በኤክስፖው ከ30 በላይ የመንግሥት ተቋማት፣ ከ40 በላይ ባንኮችና ኢኮሜርስ ድርጅቶች፣ ከ30 በላይ ኩባንያዎች እንዲሁም ከ50 በላይ የግሉ ዘርፍ የአይሲቲ ኩባንያዎች፣ የፈጠራ ሥነ-ምህዳር ገንቢና ተዋናዮች እንደሚሳተፉም ጠቁመዋል።

ዶክተር ይሽሩን አክለውም ፤ ኤክስፖው ግንቦት 10 ቀን 2016 ዓ.ም በአይሲቲ ፓርክ ይከፈታል ያሉ ሲሆን ከግንቦት 11 እስከ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሳይንስ ሙዚየም ይካሄዳል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የዓለም ሀገራት ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ ፣ ዲጂታልና ኢኖቬሽን ዘርፍ የሰጡት ትኩረት የኢኮኖሚያዊ እድገታቸው መሰረት በመሆኑ እድገቶቻቸውን በፍጥነት እያስተናገዱ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያም ይህንን ዓለምአቀፍ ሁኔታ በመገንዘብ ዘመኑን የሚመጥን ሥራ በመሥራት ከሌሎች አኩል በመራመድ በዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱንም ነው ያመላከቱት።

ዶክተር ይሽሩን፤ በኤክስፖው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በጤና፣ በትምህርት በግብርና በኢንዱስትሪ በቱሪዝምና በሌሎች ዘርፎች የሚከናወኑ የፈጠራ ሥራዎች፣ የተዘረጉ አዳዲስ አሠራሮች እንዲሁም የየዘርፉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለእይታ የሚቀርቡበት መሆኑንም አብራርተዋል።



በኤክስፖው አዳዲስ ፈጠራዎች የሚያቀርቡበትና የዘርፉ አጀንዳዎች ላይ በጋራ የሚመከሩበት እንዲሁም ሀገራዊ መነቃቃትን የሚፈጥርበት ነው ያሉት ዶክተር ይሽሩን፤ የማጠቃለያው የእውቅና እና ሽልማት መርሃ-ግብርን በማካተት ግንቦት 18 ቀን 2016 ዓ.ም በዓድዋ መታሰቢ ሙዝየም የሚከናወን መሆኑን ተናግረዋል።

# ምክክሩ ለሀገሪቱ ችግሮች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ፕሬዚዳንት ጻድቁ አብዶ ገለጹ (ፓስተር)።

የህብረቱ ፕሬዚዳንት ጻድቁ አብዶ (ፓስተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ተግባር በሀገሪቱ እስካሁን ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮችን በመለየት እና በማጥናት ምክክር እንዲደረግ ማደረግ ነው። ከዚህ መነሻነት ሀገራዊ ምክክሩ ሀገሪቱ ላሉባት ችግሮች መፍትሄ በመሆኑ ሁሉም ሊደግፈውና ሊሳተፍ ይገባል።

በህብረቱ ይህን ኮሚሽን ተቋቁሞ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን በአውንታዊ የምታይ ጉዳይ ነው ።

በሀገራዊ ምክክር የሀገርን ችግሮች መፍታትና ዘላቂ ሰላምን ማስፈን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገራት ተግባራዊ ሆኖ ውጤት አምጥቷል ያሉት ፕሬዚዳንት ጻድቁ ፤ ለዚህም ደቡብ አፍሪካ ለዚህ ማሳያ ስትሆን ምክክሩ ሀገሪቱን ከጥፋት መታደግ መቻሉን አውስተዋል።

ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሀገሪቱ ያሉባትን ችግሮች ለመፍታት መፍትሄ መሆኑን ጠቁመው፤ ሁሉም ህብረተሰብ በንቃት ሊሳተፍና ሊደግፈው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ጻድቁ (ፓስተር) ገለጻ፤ መንግሥት ይህን የምክክር ኮሚሽን ሲያቋቁም በኮሚሽኑ እንዲካተቱ የተደረጉ ሰዎች አብዛኞቹ በእውቀት፣ በሥራ ልምድ እንዲሁም በማህበራዊ ተሳትፏቸው ጥሩ ስም ያላቸው ናቸው። ይህም ለምክክሩ መሳካት ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የሚያከራክሩን ጉዳዮች ያሳለፍናቸውን ታሪኮን የምንተረጉምበት መንገድ የተለያየ በመሆኑ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ እነዚህን ጉዳዮች በምክክር በአጭሩ ካልቋጨናቸው እድሜ ልክ ከዚህ አዙሪት መውጣት ከባድ እንደሚሆን ገልጸዋል።

በሀገራዊ ምክክርና በሽግግር ፍትህ የግጭት መነሻ አጀንዳዎችን በግልጽ ተወያይተን መፍትሄ የምናስቀምጥበት፣ የተበደለ የሚካስበት፣ የበደለም ይቅርታ የሚጠይቅበት መሆኑን ገልጸው፤ በኢትዮጵያ ያሉ ሃይማኖቶች ፣ ባህሎች እና ልምዶች ችግሮችን በውይይት የመፍታትንና የእርቅን ሥርዓት የሚያስተምሩ መሆናቸው ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት እንደሚያግዙ ጠቁመዋል።

ጻድቁ (ፓስተር)፤ የሀገራዊ ምክክር እንደ ሕዝብ እስካሁን ካለፍንባቸው የግጭት አዙሪት በመውጣት ወደ መግባባት መሄድ ይኖርብናል ሲሉም ተናግረዋል።

የታጠቁ ኃይሎች ሥልጣን በኃይል ለመያዝ ከመሞከር ይልቅ ለውይይት መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ከዚህ አይነት አዙሪት መውጫ መንገዱም የጋራ መግባቢያ ጉዳዮች ላይ መመካከር የጋራ መፍትሄ ማስቀመጥ ሲቻል ብቻ መሆኑን አመልክተዋል።

# “ብልጽግና የየትኛውም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ብልጽግና በጋራ እንዳንሰራ ያደረጉንን እሳቤዎች ያፈረሰ፣ በፕሮግራምና በስትራቴጂ ደረጃ ሁሉንም ባህል፣ እምነትና ብሔር አቅፎ የሚሠራ ፓርቲ ነው። በዚህም በርካታ ሀገራዊ ለውጦችን ማስመዝገብ እንደተቻለ አመላክተዋል።

ዶክተር ዐቢይ እንዳስረዱት፤ ሀገሪቱ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ያለተቆራረጠ ዕድገት ማስመዝገቧን ተናግረው፤ በ2011 ዓ.ም 96 ቢሊዮን ዶላር የነበረውን ጥቅል ሀገራዊ ምርት በ2016 ዓ.ም 205 ቢሊዮን ዶላር ማድረስ ተችሏል። የነፍስወከፍ ገቢንም ከ922 ወደ አንድ ሺህ 822 ማሳደግ ተችሏል።

የዋጋ ንረትና ሥራ አጥነት ዋነኛ የሀገሪቱ ስብራት መሆናቸውን ገልጸው፤ ባለፈው ዓመት 33 ነጥብ አምስት በመቶ የነበረውን የዋጋ ንረት ወደ 23 ነጥብ ሶስት በመቶ ማውረድ የተቻለ ሲሆን፤ እስከ ሰኔ መጨረሻ ወደ 20 በመቶ ለማውረድ ታቅዷል ብለዋል።

ምግብ ነክ የዋጋ ንረትን ከ31 ነጥብ ስምንት በመቶ ወደ 27 በመቶ ምግብ ነክ ያልሆነውን የዋጋ ንረት ደግሞ ከ36 በመቶ ወደ 18 በመቶ ማውረድ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ሰፊ ሥራን ይጠይቃል ሲሉ አመላክተዋል።

ከተመዘገበው ዕድገት ውስጥ የግብርናን ለአብነት አንስተው፤ ባለፈው ዓመት 393 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት ማምረት የተቻለ ሲሆን፤ በዘንድሮው ዓመት 506 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት መቻሉን ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂን በሚመለከት የባለፈው ዓመት በዲጂታል ክፍያ የተፈጸመው ሁለት ነጥብ ስምንት ዘጠኝ ትሪሊዮን እንደነበር አስታውሰው፤ ዘንድሮ በሶስት እጥፍ አድጎ ስድስት ነጥብ ሰባት ትሪሊዮን ደርሷል። በተያዘው ዓመት የጥሬ ገንዘብ ዝውውር በዲጂታል ክፍያ ተፈጽሟል ብለዋል።

የመንግሥት ገቢና ወጪን በሚመለከት ባለፈው ዓመት ዘጠኝ ወራት 324 ቢሊዮን የነበረው የሀገር ውስጥ ገቢና የወጪ ንግድ ገቢ በዘንድሮ ዘጠኝ ወራት 374 ቢሊዮን መግባቱን ጠቁመው፤ ገቢን ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በግብርና የሜካናይዜሽንና የክላስተር ሥራን ማስፋፋትና ምርታማነት በመጨመር፣ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የግል ሴክተሩ በነጻ የንግድ ቀጣናው እንዲገቡ አስቻይ ሁኔታን በመፍጠር፣ በንግድና አገልግሎት ደግሞ ካፒታል ገበያ፣ በስታርት አፕ፣ በዲጂታል ኢኮኖሚና መሠረተ ልማት ላይ ከሠራን ይበልጥ ማደግ እንችላለን ሲሉ አብራርተዋል።

በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የማክሮ ኢኮኖሚውን ስብራት መጠገን፣ የኢንቨስትመንት ፍሰትን፣ ምርታማነትንና የመንግሥትን ተቋማዊ አቅም በማሳደግ ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

ሥራ አጥነት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ያልዘመነ የገበያ ሥርዓት፣ የጥቁር ገበያ መስፋፋት፣ ያልዳበረ መሠረተ ልማት፣ ዝቅተኛ የምርት ጥራትና የዓለም አቀፍ ገበያው መዋዠቅ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተግዳሮት መሆኑን ገልጸው፤ ኢኮኖሚውን ከነዚህ ችግሮች ለማስወጣት በቅንጅት መሥራት ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከግብርናው ዘርፍ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን!

የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ምርት እና ምርታማነትን አሳድጎ ሀገር እና ሕዝብን ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ ለማድረግ የለውጥ ኃይሉ ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ቢሆንም እያስመዘገበ ያለው ስኬት በብዙዎች ዘንድ ከበሬታ የተቸረው ሆኗል።

በምግብ እህል ራስን ለመቻል ለተጀመረው ሀገራዊ መነቃቃት አቅም እንዲሆን፤ የግብርናው ዘርፍ በሀገሪቱ ተግባራዊ እየሆነ ባለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ነው። ዘርፉን በሁለንተናዊ መልኩ ማዘመን ወሳኝ መሆኑ ታምኖበትም ወደ ሥራ ከተገባ ውሎ አድሯል።

ለዚህም የግብርናውን ዘርፍ ሜካናይዝድ ከማድረግ ጀምሮ በጥናት እና በምርምር የታገዘ እንዲሆን በርከት ያሉ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፤ የበጋ ስንዴን ጨምሮ እንደ ሀገር በዘርፉ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች ዓለም አቀፍ እውቅና እስከ ማግኘት መድረሳቸው የዚሁ እውነታ ተጨባጭ ማሣያ ነው።

አዳዲስ የእርሻ መሬቶችን ወደ ሥራ ከማስገባት ጀምሮ ቀደም ሲል ሥራ ላይ የነበሩ የእርሻ መሬቶች በተሻለ ምርታማ የሚሆኑበትን መንገድ በጥናት በማፈላለግ የተሄደበት ረጅም ርቀት፤ አርሶ አደሩን የተሻለ ተጠቃሚ ከማድረግ ባለፈ ሀገርን በክፉ ወቅት መታደግ ያስቻለ ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል።

ሀገር ብዙ ፈተናዎችን እያለፈች በነበረው ሁኔታ ውስጥ በዘርፉ የተመዘገበው ስኬት ፤ ዘርፉን በተሻለ መንገድ መመራት ከተቻለ እንደ ሀገር ትልቅ ተስፋ ያለው ፣ ሀገርን ከተመጽዋችነት / ከጠባቂነትለመታደግ ለተጀመረው ሀገራዊ መነቃቃት ትልቅ አቅም እንደሚሆን በተግባር ያመላከተ ነው ።

ይህንን ታሳቢ በማድረግ መንግሥት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ በጊዜው እንዲደርስ እያደረገ ያለው ጥረት ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ዛሬ ላይ የደረሰበት ደረጃ የሚበረታታ እና ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት በተጨባጭ ያሳየ ነው።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ለ2016/17 የበልግና የመኸር ወቅት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከ19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶ ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚሆነው ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ይገኛል፡፡ በምርት ዘመኑ አገልግሎት ላይ እንዲውል ከተገዛው የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ 25 በመቶ የሚሆነው ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፤ 20 በመቶ የሚሆነው ለበልግ፤ 55 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ለመኸር እርሻ የሚውል ነው።

በ2014/15 የምርት ዘመን የተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር በ2016/17 እንዳይከሰት የግዥ ሥርዓቱን የማሻሻል፤ አስቀድሞ የመግዛት፣ ስርጭቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ ተሠርቷል፤ ይህ በመደረጉም በቂ የአፈር ማዳበሪያ ለበልግ እንዲቀርብ አስችሏል፡፡

ከዚህ በፊት ከሚገዛበት በዘንድሮው ዓመት ቀደም ብሎ አፈር ማዳበሪያው እንዲገዛ መደረጉ ጊዜና ጉልበትን ከመቆጠቡ ባለፈ አርሶ አደሩ ተረጋግቶ ግብዓቱን በሚፈልገው ሰዓት በቀላሉ እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡ ስርጭቱ ላይ ሕገ ወጥ አሰራሮች እንዳይኖሩም የሚከታተልና የሚቆጣጠር ግብረ ኃይል ተቋቁሙ ወደ ሥራ መግባቱ፤ ስርጭቱ ላይ የጎላ ችግር እንዳይከሰት አድርጓል፡፡

የግብርና ሜካናይዜሽና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እየተሠራ ባለው ሥራ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፤ በበልግና በመኸር እርሻ ላይ ከ15 ሺህ በላይ ትራክተሮች ጥቅም ላይ ውለዋል፤ ለቀጣይ የመኸር እርሻ ቁጥራቸውን በማሳደግ ጥቅም ላይ የማዋል ተግባር እየተከናወነ ነው ፡፡

በስንዴ፣ ቡና፣ ሩዝና ሻይ ምርቶችና በአረንጓዴ ዐሻራ የተከናወኑ ሥራዎችም በርካቶች አድናቆታቸውን የቸሯቸው ሲሆኑ፤ በኢነርጂና በሰው ኃይል ያሉ አቅሞችም ለኢንዱስትሪ ምርታማነት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መናገራቸው ይታወሳል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል፤ ይህም የአምራች ዘርፉን በማጠናከር የተሻለ ዕድገት ለማምጣት የሚረዳ ውጤት ነው።

የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎችን ማለትም ትራክተሮች፤ ኮምባይነሮችና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ በማኅበራትና በአርሶ አደሮች እንዲገቡ መደረጉ በዘርፉ ለሚደረገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ትልቅ አቅም እንደሚሆንም ይታመናል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአመራሩ ብቻ ሊፈቱ አይችሉም

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ምንም ይሁን ምን የመልካም አስተዳደር ንቅዘት ባለበት ሁሉ የሕዝብ ጫንቃ መቁሰሉ፤ ሕሊናም መድማቱ የማይቀር ነው:: ባላደጉ ሀገራት ውስጥ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማምጣት ሲታሰብ ፊት ለፊት እንደ ተራራ ተደንቅሮ የማይገፋና የማይናድ የሚሆነው ይሄው የመልካም አስተዳደር ችግር ነው::

መልካም አስተዳደር ማለት መልካም አስተዳዳሪ ማለት አይደለም:: ምክንያቱም መልካም አስተዳዳሪ ስላለ ብቻ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን አይቻልምና:: የራሱ የጦር ብቃትና ስልት ያለው አንድ የጦር መሪ የግል ብቃት ስላለው ብቻ አሸናፊ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ ጎበዝ የጦር መሪ፤ ጎበዝ ወታደሮች ሊኖሩት ግድ ነው::

የመልካም አስተዳደር ሥርዓትም እንዲሁ ነው:: አንድ ጠንካራ አመራር ብቻውን መልካም አስተዳደርን ያሰፍናል ተብሎ አይታሰብም:: መልካም አስተዳደርን ማስፈን የብዙዎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው:: በመልካም አስተዳደር ጉዳይ አመራሩ ብቻውን ሊታገልም ሆነ ሊጠየቅ ይችላል ወይ? በለማ ቁጥር "ጎሽ!"፤ በተበላሸ ቁጥርም "አይንህ ላፈር!" የምንለው መሪውን ብቻ ከሆነ ከምናቃናው ይልቅ የምናጣምመው ይበልጣል::

ችግሩ የሚደርሰው ሕዝብ ላይ እንደመሆኑ፤ ሕዝብ ይህን አጥርቶ የሚመለከት አይንና የሚታገልበት ወኔ ሊኖረው ይገባል:: አብዛኛዎቹ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፤ መብትና ግዴታን ጠንቅቆ ካለማወቅ የሚፈጠሩ ናቸው:: ሕዝብ መብቱን ተረድቶ የማይጋፈጥ ከሆነ የችግሩ ሰለባ ከመሆን አይድንም:: በመልካም አስተዳደር ችግር ውስጥ፤ ከታች ያለው ሠራተኛና ሕዝቡም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዐሻራቸው መኖሩ አይቀርም::

በየተቋማቱ መውጫና መግቢያ በር ላይ የተለጠፉት የመልካም አስተዳደር መርሆዎች በአመራሩ ብቻ ሳይሆን በታችኛውም ሠራተኛ ልብ ውስጥ መስረጽ ይኖርባቸዋል፤ ወደ ሕዝቡም መውረድ አለባቸው:: አንድ ሰው አገልግሎት ፍለጋ ወደ አንድ ተቋም ሲሄድ አገልግሎቱን የማግኘት መብት እንዳለው ጠንቅቆ ቢያውቅ ኖሮ የሻይና የሥራ ማስኬጃ እያለ ወደ ኪሱ ባልገባ ነበር::

የመልካም አስተዳደር ችግር "የሕግ የበላይነት" የሚለውን ወሳኝ መርህ ካለመገንዘብ አለበለዚያም ከማናለብኝነት የሚመነጭ ነው:: ሕግ የበላይ አልሆነም ማለት በጭንቅላት ቆሞ ለመጓዝ እንደመሞከር ነው:: ይህ ደግሞ ከመውደቅም በዘለለ ከፍ ያለ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል:: አመራሩ የሕግ የበላይነትን አክብሮ ሲሠራ፤ ሰራተኛውም ሕግን አክብሮ ይሠራል፤ ሕዝብንም በአግባቡ ያገለግላል:: ይህ ሲሆን ችግሮች መግቢያ ቀዳዳ አይኖራቸውም::

የመልካም አስተዳደር ግድፈት ማለት በተዘዋዋሪ የሰብዓዊና ሕጋዊ መብቶች ጥሰት ነው:: ሰብዓዊ መብት፤ ከሀገሪቱ ሕገ መንግሥት አልፎም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያስጠይቅ ነው:: ሁለቱም ድርጊቶች፤ ወንጀል ስለመሆናቸው በሕገ መንግሥታችን ውስጥ የተደነገጉ ቢሆንም፤ ከመልካም አስተዳደር ጉድለት አንጻር የሚከሰቱ ጥሰቶችን በተመለከተ በቂና ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራሪያ ተሰጥቷል ለማለት ያዳግታል::

አሻሚነታቸው ከፍ ያለ ነው:: ምክንያቱም የመልካም አስተዳደር ችግሮች፤ መልካቸውን እየቀያየሩ ከመምጣታቸውም በላይ ውስብስብና አንዳንዴም በሕግ ፊት መረጃና ማስረጃ የማይገኝላቸውም ጭምር በመሆናቸው ነው:: ተበዳዩም ቢሆን እንደሌሎች ወንጀሎች ይህን ይዞ ለሕግ አቤት ለማለት ምቹ ሁኔታን አይፈጥሩለትም:: ቢቀርብም ፍሬቢስ ከሆነ ውንጀላነት ላያልፍ ይችላል::

የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጣሪ የሚሆኑትን ሰዎች እያደኑ ችሎት ከማቆም ይልቅ፤ የሕግ ፊደል ማስቆጠሩ ቀላሉ መፍትሄ ነው:: ካጠፉ በኋላ እየቀጡ ከማስተማሩ፤ ከጥፋቱ በፊት ሁሉን ማስገንዘቡ፤ ለመልካም አስተዳደር መልካምነት ይበጃል:: ሕግ አስፈጻሚው አካልም ከየትኛውም በበለጠ ከሕዝባዊ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት አካባቢ አይኑን ሊነቅል አይገባም:: በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ ስለተቀመጡት ጉዳዮች፤ አስተዳደርና ሠራተኛው ምን ያህል ተገንዝቦታል የሚለውን መፈተሽም ሆነ በጋራ መሥራት አለበት::

የመልካም አስተዳደር ችግር፤ ትልቁ እልፍኝ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው:: ችግሩ በግልም ሆነ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ሊፈጠር የሚችል ቢሆንም በመንግሥት ተቋማት ግን ይብሳል:: የመልካም አስተዳደር ችግር ተብሎ ሲነሳም በሙስናና መሰል ነገሮች ውስጥ የምንመለከታቸውን ትላልቆቹን ካልሆነ በቀር ከስር ያሉት ጥቃቅኑ ትዝም አይሉንም::

በከፍተኛ ሁኔታ የሚመዘምዙን ግን፤ ንቀን የምናልፋቸው ትንንሾቹ ናቸው:: አንዳንዴም መብትና ግዴታ አገልጋይና ተገልጋይ፤ የተገላቢጦሽ የሚዘበራረቅባቸውም ጭምር ናቸው:: የምንፈልገውን ላለማጣት ስንል ብቻ መብታችንን አሳልፈን እንሰጣለን:: "ለምን?" ብሎ መጠየቅ ፈጽሞ ክልክል ይመስለናል:: ችግር ፈጣሪዎቹ መብታችንን እንደ ግዴታ ቆጥረው ይነጥቁናል:: የእነርሱም ግዴታ የእነርሱ መብት ብቻ ይሆናል::

የሕዝብና ለሕዝብ በሆኑ ስፍራዎች በጥቂት ጉልበተኞች ምክንያት ብዙዎች መብት አልባና ግዞተኛ ሆነው የሚታዩበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም:: ለምሳሌ ወደ መናኸሪያዎች ጎራ ስንል የምንመለከተው ምንድነው? ከሕጉና ከሕዝቡ በላይ መብቱ በባለንብረቱ መዳፍ ስር የሚሆንባቸው ሁኔታዎችን፤ አጋጣሚ ናቸው ብለን ማለፍ አንችልም::

ለምሳሌ አንድ የትራንስፖርት መኪና ላይ የሚሠራ ረዳት ከመንገድ ላይ ሊጠብቁት የሚችሉትን የትራፊክ ፖሊሶችን እያሰበ፤ ገና ጉዞ እንደጀመረ የሃምሳና የመቶ ብር ኖቶችን በተለያየ ኪስ ለብቻው ማስቀመጥ የተለመደ ነው:: ለዚህም ከታሪፉ በላይ እስከ አርባና ሃምሳ በመቶ ድረስ በእያንዳንዱ ምስኪን ተሳፋሪ ጭማሪ በማድረግ የቦተረፈውን ገንዘብ፤ ተባብረን እንዝረፍ ለሚለው ትራፊክ ያጎርሳል:: በዚህ አጋጣሚ መልካምና ለሕዝብ አሳቢ፤ ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ አገልጋይ እንዳለም ታሳቢ ይደረግ::

መንግሥት አምኖ ያቆመው ሕግ አዋቂ ሰው በብልሹ የመልካም አስተዳደር ተግባር አብሮ መዝረፍን ከመረጠ ሾፌርና ረዳት ሕዝብን ቢመነትፍ እንዴትስ ይፈረድበታል? የቁጥጥር መሥሪያ ቤቱ ይህን ማጽዳት የግድ ይለዋል:: አለበለዚያ መልካም አስተዳደር...የሕዝብ አገልጋይነት.... የሚል ዲስኩር ቢሰማ፤ ዋጋም ለዛም የለውም::

የህክምና ተቋማትና ባለሙያዎች፤ የሕዝቡ ነብስ በአደራ የተቀመጠባቸው፤ የፈጣሪ እጆች ናቸው:: "ጤና ይቀድማል" የሚለው ሕዝብ፤ ከምንም በላይ እኚህ ተቋማት አንዳች እክል እንዲገጥማቸው አይፈልግም:: ይህን ያህል በህይወቱ የመጀመሪያና ወሳኝ ስፍራ አድርጎ ከሚቆጥረው ሥፍራ በቂ አገልግሎት ያገኛል ለማለት አይቻልም::

ባደጉት ሀገራት አንድ ዶክተር ለአንድ ሰው በሚመድቡበት በዚህ ዘመን በእኛ ሀገር ሁኔታ አንድ ዶክተር በበርካታ ሰዎች የተከበበ ነው:: ይሁንና እዚህ አካባቢ፤ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚታይ ከሆነ ሕዝቡ አበቃለት እንደማለት ነው:: አሁንም ከጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች እስከ ዶክተሮቹ ድረስ፤ በመልካም ስነምግባር ማህበረሰቡን የሚያገለግሉ እንዳሉ አንርሳ::

ነገር ግን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የራሱን ሆድና ኪስ ለመሙላት የሚያደፍጥ ምግባረ ብልሹ በየትኛውም ቦታ አይጠፋም:: በጤና ተቋማት ውስጥ መድኃኒት እያለ አልቋል በማለት ታካሚዎች ውጪ ካለ የግል መድኃኒት መደብር እንዲገዙ ጥቅም የሚጋሩበትን ቤት የሚጠቁሙ የጤና ባለሙያዎች አጋጥመውን ይሆናል::

ተምረዋል የምንላቸው አንዳንድ የጤና ባለሙያዎች ውስጣቸው እያወቀው፤ አላስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ምርመራዎችን እንድናደርግ በወረቀት ማዘዣ ጫር ጫር በማድረግ ወደ አንደኛው የግል የህክምና ተቋም ይልኩናል:: ሁልጊዜም ባይሆን፤ ከግል ሀኪም ቤቶች ጋር በመመሳጠር በዚህ አይነት መልኩ የሚጎራረሱ የህክምና ባለሙያዎችና ተቋማት ስለመኖራቸው የሚካድ አይደለም::

እንዲህ ዓይነቶቹ በባለሙያው ውሳኔና ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ ጉዳዮች ከሕግና ደንብ ይልቅ በባለሙያዊ የሞራል ህሊናና ሰብአዊነት ላይ የተደገፉ ናቸው::

የባለሙያውን የኋላ ግድፈት በቅጣት ለማስተካከል ከማድፈጥ ይልቅ፤ አስቀድሞ ውስጣዊ ማንነቶቹን መገንባቱ ብልህነት ነው:: ግለሰባዊ ንቅዘቶች እንዲህ እያሉ ወደ አስተዳደራዊ ንቅዘት ያመራሉና::

መልካም አስተዳደርን አጎልብቶ፤ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ለማቆም ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል:: ችግሩ የሚፍጠርባቸው አካባቢዎች ላይ ብቻ ከማተኮር፤ ከታች ገና እየመጡ ያሉት ላይ መሥራት ወሳኙ ነጥብ ነው:: ችግሮቹ የሚፈጠሩት ከማህበረሰባዊና ከሰብአዊ እሴቶች እጦት ነውና መላውን ትውልድ ለመሥራት፤ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በበቂ ማካተትም ሊታሰብበት ይገባል::

# ተጠየቅ

# “የሚዛን አማን አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሲጠናቀቅ የዞኑንና የክልሉን ሁለንተናዊ ገጽታ ይቀይራል”

- አቶ ሀብታሙ ካፍትን
በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የቤንች ሸኮ ዞን አስተዳደር

**በሞገስ ተስፋ፣ ሙሉቀን ታደገና**
**መክሊት ወንድወሰን**


ፎቶ- በረሁን ታደሰ

የቤንች ሸኮ ዞን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ከሚገኙ ስደስት ዞኖች አንዱ ነው። የዞኑ መቀመጫ የሆነችው ሚዛና አማን ከተማ ከአዲስ አበባ በ585 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፤ በ6 ወረዳዎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረች ነች። ዞኑ በማር፤ በቡና፤ በቅመማ ቅመምና በሌሎች የግብርና ዘርፎች እምቅ ሀብት እንዳለው ይነገራል። ካለው ሀብት አንጻር የዞኑ ሕዝብ ያለው የልማት ተጠቃሚነት፤ የመልካም አስተዳደር፣ የትምህርት፣ የጤና ተደራሽነትና መሰል ጉዳዮች ላይ ከዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሀብታሙ ካፍትን ጋር ቆይታ አድርገናል። እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ እንደ ክልል ከተዋቀረ አንስቶ በዞኑ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** የቤንች ሸኮ ዞን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን ሚዛን አማን ከተማን ማዕከል አድርጎ የተመሰረት ነው። በዞኑ ሸኮ፣ ጉራፋርዳ ፣ ደቡብ ቤንች ፣ ሰሜን ቤንች፤ሼ ቤንች ፣ ሲስካ ከተማ አስተዳደር፤ ሚዛን አማን እና ጊቤንች በሚባሉ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ስድስት ወረዳዎች በአጠቃላይ ስምንት ወረዳዎችን በስሩ የያዘ ነው።

ክልሉ እንደክልል ሲመሰረት ሕዝቡ በርካታ የልማት ጥያቄዎች ያነሳ ነበር። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ መጀመሪያ በክልል፤ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የመለየት ስራዎችን አከናወነ። ቀጥሎም ጥያቄዎችን ኢኮኖሚ ፣ ማህበራዊና እና ፖለቲካዊ በሚል በዘርፍ የማስቀመጥ እና የመለየት ሥራዎችን አከናወነ። በልየታው መሰረት ወደ ሥራ ገባን። ይህም የህብረተተሰቡን ጥያቄዎች ሁሉንም ባይሆን አብዛኛውን መፍታት አስችሎናል።

የቤንች ሼኮ ዞን ለክልሉ በግብርናው እና በማዕድን ዘርፉ ዋና የኢኮኖሚ ስበት ማእከል ነው ብለን እናምናለን። ይህን ሀብት በዘላቂነት ለማልማት እና ለመጠቀም ደግሞ ከምንም በላይ ሰላም እና መረጋጋት ወሳኝ ነው። በመሆኑም በኢኮኖሚ ፣በማህበራዊ፣ በፖለቲካና በአስተዳደር ዘርፍ ያሉ ልዩነቶች በማጥብብ አንድነቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠል ፣ የቀጣናውን ሰላም በዘላቂነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ቁልፍ፣ቁልፍ ተግባራትን በስፋት ተከናውነዋል።

ለአብነት ያህል በኢኮኖሚው ዘርፍ በግብርናው ላይ የተለያዩ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይቷል፤ እየተከናወኑም ነው። በግብርናው ዘርፍ የቡና፣ የቅመማ ቅመም፣ ዓመታዊ ሰብል እና ማር በዞኑ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ይመረታሉ። በ2013-2014 ዓ.ም የምርት ዘመን ዞኑ ከ30ሺ ቶን በላይ ቡና ለማዕከላዊ ገበያ አቅርቧል። ይህን ለማስቀጠል በማሰብ በዘንድሮው ዓመት በርካታ የቡና ችግኞችን ለመትከል ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጓል፤ ያረጁ እናት የቡና ተክሎችን የማስጎንደል ሥራ ተሠርቷል፤ በተጨማሪም በቡና ጥራት ላይ የቡና አሰባሰብ፣ ክምችትና ግብይት ላይ ከፍተኛ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በቅመማ ቅመም ዘርፍ (ቁንዶ በርበሬ፤ ሔል፤ እርድ፤ ኮረሪማ እና መሰል ቅመማ ቅመሞችን) በከፍተኛ ደረጃ ለማእከላዊ ገበያ የሚያቀርብ ዞን ነው። በዚህ ዘርፍ ባለሀብቶች እና አርሶ አደሮችም በስፋት እየተሳተፉ ይገኛሉ። ዞኑም ምርቱን የማስፋት እና ጥራቱን የማስጠበቅ ሥራ እያከናወነ ነው።

ሌላው በግብርናው ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራባቸው ከሚገኙ መስኮች አንዱ የፍራፍሬ ምርት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በዞኑ የሙዝ ማሳዎችን ጫካ በሚባል ደረጃ በኩታ ገጠም በማረስ በርካታ ሺህ ሄክታር መሬትን እየለማ ይገኛል። ከሙዝ በተጨማሪ በዞኑ የአቮካዶ ምርት በከፍተኛ ደረጃ እየተመረተ ነው።

ቀደም ሲል የነበረው የአቮካዶ ዝርያ ለዘይት ምርት ጥሩ ስላልነበር አሁን ላይ በተሻሻሉ የምርጥ ዘሮች ተተክተዋል። ይህም ከአቮካዶ ፍሬ ዘይት ያመርት ለነበረው የጅማ ዞን ኢንዱስትሪያል ፓርክ ምርት በማቅረብ ኢንዱስትሪያል ፓርኩ የነበረበትን ከፍተኛ የግብዓት ችግር መፍታት ተችሏል። አሁን ላይ አቮካዶን በንቅናቄ ለማልማት የዘመቻ ሥራዎች ተጀምረዋል።

ዓመታዊ ሰብል በተመለከተ በቆሎ፣ ሩዝ እና መሰል ሰብሎችን እያመረትን ነው። ለአርሶ አደሩም የምርጥ ዘር፤ ማዳበሪያና ሌሎችን ግብአቶች በማሟላት ላይ እንገኛለን። ከ20ሺ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያዎችን ማሰራጨት ተችሏል። በዘንድሮው የበልግ ወቅት ብቻ ከ90 ሺህ ሄክታር በላይ የበቆሎ ማሳዎችን ማልማት ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- የቡናና ሻይ ባለስልጣን በሚያርገው የቀጥታ የገበያ ትስስር ቡና ለዓለም ገበያ እየቀረበ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ይህ አሰራር አምራቹን እና ነጋዴውን ለከፍተኛ ኪሳራ እየዳረገ መሆኑ ይነገራል። ይህ ምንያህል እውነት ነው ?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** የቀጥታ ትስስሩ እንደተጀመረ በነበሩት ዓመታት በተለይም በ2013-2014 ዓ.ም የምርት ዘመን በቡና ግብይቱ ጥሩ ውጤት ተገኝቶ ነበር። ነገር ግን አሁን ላይ የቀጥታ የትስስር ግብይት ሥርዓት በቡና ግብይት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ነው። አርሶ አደሮች በየጊዜው ወደ ቢሮ በመምጣት ቡናቸው ተወስዶ ክፍያ እንዳልተፈጸመላቸው ይናገራሉ። በቡና ግብይት ሥርዓቱ ላይም እኛም እንደ ዞን እየተቸገርን ነው።

ከዚህ ቀደም ግብይቱ የሚፈጸመው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ኢ.ሲ.ኤክስ) ነበር። በዚህም አንድ የቡና አልሚ ለቡና ገዥው ሲሸጥ አቅራቢውም ኤክስፖርተሩም ሁለቱም ይታወቃሉ። ቡናውም ደረጃ ስንት እንደሆነ ይታወቃል። ከደረጃ በመነሳትም ቡናው ለሀገሪቷ ገቢ ማስገኘት ይችላል አይችልም የሚለውም ይታወቃል። ቡናው ከሀገር ውጭ ሲላክም ወዴት ሀገር እንደተላከ ምን ያህል ገቢ እንዳስገኘ ይታወቃል።

ይህንንም መረጃ በመያዝ ቡናው ከደረጃ በታች እንዲሆን ያደረጉ ሰዎችን በመያዝ ማጠቢያ ማሽኑን በመለየት፤ ማከማቻው ከማን እንደሚረከብ በመጠየቅ የተለያዩ ስልጠናዎችም ይሰጣቸው ነበር። አሁን ግን ግብይቱ በምርት ገበያ ስለማይፈጸም ከላይ የተጠቀሱትን ልየታዎች ለማከናወን ተቸግረናል።

በተጨማሪም ቡና በኢሲኤክስ ሲሸጥ ምን ያህል ምርት ከየት አካባቢ እንደሚሰበሰብ የመለየት ሥራ ይከናወን እና ወረዳዎች ለማእከላዊ ገበያ ባቀረቡት ልክ ነጋዴዎች ለወረዳው ገቢ ያስገባሉ። በገባው ገቢም ወረዳዎች የተለያዩ የልማት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይደረግ ነበር። አሁን ላይ ግን ነጋዴዎች እና ግለሰቦች እንኳን ለወረዳው ገቢ ሊያስገቡ ይቅርና ምርቱን ለሚያቀርብላቸው ገበሬም ክፍያ መፈጸም አልቻሉም። ምክንያቱም በቀጥታ ትስስር በሚደረገው የግብይት ሥርዓት ነጋዴዎች ከሸጡት ቡና ብር ማግኘት አልቻሉም።

ለምሳሌ ሸኮ ወረዳ 29 ሚሊዮን ማግኘት ከነበረበት ገቢ ውስጥ ያገኘው 9 ሚሊዮን ነው። በዚህም አርሶ አደሮች ፣ ነጋዴዎች እና ዞኑ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብተዋል።

**አዲስ ዘመን ፡- በቀጥታ ትስስሩ ከነጋዴዎች ተረክቦ ወደውጭ የሚሸጠውን ሰው ነጋዴዎች እንደማያውቁት ይናገራሉ። በተጨማሪም በሀገሪቱ ያለው የነጻ ገበያ ሥርዓት ነው ቢባልም —ኢሲኤክስ“ በፈለገው ዋጋ መግዛት እንዳይችል በመከልከሉ አምራች ገበሬዎች እና ነጋዴዎች አማራጭ ገበያ እንዳይኖራቸው እና ብድር ማግኘት እንዳይችሉ ማድረጉ ይነገራል። በዚህ ላይ ምን ይላሉ ?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በዚህ ጉዳይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቻለሁ። ነገር ግን ይህ አሰራር በፖሊሲ የተቀመጠ አቅጣጫ ነው። መስተካከልም ያለበት ነው። ዞኑ ከፍተኛ የቡና ምርት ለገበያ አቅራቢ እንደመሆኑ የቡና ጥራትን የማስጠበቁን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እያከናወነ ነው። ይሁን እንጂ አሁን ባለው የቡና ግብይት ሥርዓት የነጋዴው ኢኮኖሚውም ሆነ ህይወቱ ተዛብቷል። አርሶ አደሮችም ተሰብረዋል። በዩኒየንና በአርሶ አደር፣ በአርሶ አደርና በነጋዴ መካከል ያለው ትስስርም ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ገብቷል።

እኔን በጣም እያሳሰበኝ ያለው ቀጥታ ትስስሩ በፈጠረው ችግር ምክንያት ከዚህ ቀደም ለማእከላዊ ገበያ ይቀርብ የነበረው ቡና አሁን ላይ የት እንደሚገባ አለመታወቁ ነው። በአንጻሩ ሀገሪቱ ኢኮኖሚዋን ለመጠገን እና ገበያውን ለማረጋጋት እንዲሁም የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ ዶላር የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ነች። ይህ ችግር ሲጨመር ደግሞ ነገሮችን ከባድ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ቡና በሀገር ውስጥ ገበያ ሲሸጥ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አይቻልም።

አሁን ያለው አሰራር የሀገርን፣ የአርሶአደርን እና የነጋዴን ኢኮኖሚ የሚጎዳ ሆኖ ነው ያገኘነው። የማን ቡና ጥራት አለው፤ የማነው የሌለው የሚለውን ለማወቅ የሚያስችለውን አሰራር የተወሳሰበ አድርጎታል። አጠቃላይ ጉዳዩ ለዚህ ቀጣና አደገኛ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የዞናችሁ ገበሬዎች እና ነጋዴዎች ለማእከላዊ ገበያ ብዙ ሺህ ቶን ቡና ቢያቀርቡም ያቀረቡት ቡና ግን የዚህ አካባቢ ተብሎ ስም እንደሌለው ቅሬታ ያቀርባሉ። ለምንድን ነው ስም ያልተሰጠው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** እኔ ቡና ዘርፉ ላይ የቆየሁ ባለሙያ ነኝ። ይህ የስም ጉዳይ የረጅም ጊዜ ፈተና እና መመለስ ያልቻለ ጥያቄ ነው። ማንን እንደሚጎዳ ባላውቅም በተደጋጋሚ ጥያቄው ይቀርብ ነበር። እየቆየ ሲሄድ አንድ መፍትሄ ተብጅቶ ነበር። ይህም ዩኒየኖችን በአካባቢው ስም በመፍጠር ቡናውን በዩኒየኖች ስም መሸጥ የሚል ነበር። ነገር ግን አሁን ላይ የቀጥታ ትስስር በፈጠረው ችግር ዩኒየኖቹ በከፍተኛ ደረጃ ተዳክመዋል። ሥራ ያቆሙም አሉ።

የግብይት ሥርዓቱ ዩኒየኖቹ የባንክ ብድር ለማግኘት ተጽእኖ ፈጥሮባቸዋል። ለምሳሌ የቤንች ማጂ ጫካ ቡና እና የቤንች ማጂ አንድነት ዩኒየን ቡና ‹‹ብራንድ›› ሆኖ ነበር። ብዙ አርሶአደሮች ፈረንሳይ፤ ጀርመን፤ አሜሪካ ድረስ ሄደው ትስስር ፈጥረው ነበር። አሁን ላይ ዩኒየኖች ብድርና ሥራ ማስኬጃ በማጣታቸው እየፈረሱ ‹‹ኮላፕስ›› እያደረጉ ነው። በዚህ ጉዳይ አሁንም ለማእከላዊ ገበያ የሚቀርበው ቡና ‹‹በብራንዱ›› እንዲሸጥ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን ፡- አሁን ባለው የቡና ገበያ ሥርዓት የቡና ቅምሻ የሚያከናውኑ እና ደረጃ የሚሰጡ ተቋማት በቅርበት ባለመኖሩ ነጋዴዎች ሳልተፈለገ ወጪ እና እንግልት መዳረጋቸውን ይገልጻሉ። በዚህ ሳይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** የነጋዎች ቅሬታ ትክክል ነው። በዚህ ዞን ከፍተኛ የቡና ምርት ይገኛል። 30 ሺህ ቶን ቡና ከዚህ ተጭኖ ወጥቶ ሌላ ቦታ ደረጃ እና ስም እንዲወጣለት ከማድረግ እዚሁ ደረጃ ወጥቶለት ቢሄድ ወጪ ከመቀነስ አንጻር ጥሩ ነው። እዚህ የደረጃ መስጫ ማእከል ቢኖርም ጥሩ ነው። ለነጋዴዎችም ወጪ ቆጣቢ ነው። ከዚህ በፊት ኢሲኤክስ ደረጃ መስጫ እዚህ ከፍቶ ነበር። አሁን በተፈጠረው የግብይት ሥርዓት ማእከሉ የለም።

ማእከሉ ባለመኖሩ አሁን ላይ ከዚህ ዞን ቡና ጭነው የሄዱ ተሽከርካሪዎች የጫኑት ቡና ደረጃ እስከሚያገኝ እና የቡናው እርጥበት እስከሚቀንስ ተብሎ ሁለት ሶስት ወራት የሚጠብቁበት ሁኔታ አለ። በዚያ ጊዜ ለእያንዳንዱ ቀን ተሽከርካሪው ለቆመበት የሚከፍለው ነጋዴው ነው። ይህ ደግሞ ለከፍተኛ ኪሳራ የሚዳርግ እና ነጋዴውን ከገበያ የሚያስወጣ ነው።

በዞኑ በርካታ ቡና አልሚዎችና ምርት መኖሩን ታሳቢ በማድረግ እና ነጋዴውም በቅርበት ምርቱን ደረጃ አስወጥቶ እንዲሸጥ የደረጃ ማእከል መገንባት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን ፡- በቅመማ ቅመም እና ማር ምርት የንግድ ሥርዓት ባለመፈጠሩ አምራቾች ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻሉ ይነገራል። ይህ ምንያህል እውነት ነው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በዞኑ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች በስፋት ይመረታሉ። ነገር ግን ደረጃ/ ስታንዳርድ ወጥቶለት ለምርት ገበያ (ኢሲኤክስ) ማእከል ለግብይት አልቀረበም። ባለሀብቶች ሲመጡም ሰብልና ቡና የማልማት ጥያቄ ይዘው ነው የሚመጡት። ቅመማ ቅመምን በኢንቨስትመንት ደረጃ ለማልማት የመጣ ባለሀብት የለም።

ዛሬ ላይ ግብርና አርሶ መኖር ብቻ አይደለም ንግድ ነው። የትኛውን ባመርት ፣ የትኛው ያዋጣኛል? ተብሎ ነው የሚሰራው። አምራቾች በአርሶአደር ደረጃ ነው ያሉት። ምርቱ ሲሰበሰብ ግን ከፍተኛ ነው። በዚህ ላይ የገበያ ትስስር ከመፍጠር አኳያ ክፍተት አለ። እስካሁን

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ተጠየቅ

## “የሚዛን አማን አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሲጠናቀቅ...

ከገጽ 6 የዞረ

ያለው ትስስር ደካማ ነው። በቀጣይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይህን ችግር መፍታት እንዳለብን ይሰማኛል።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ያለው የጤና ጣቢያ ተደራሽነት ምን ያህል ነው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በጤናው ዘርፍ ከተደራሽነት አንጻር የመሰረተ ልማት ተደራሽነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በመባል ይከፈላል። ከመሰረተ ልማት ተደራሽነት አንጻር በዞናችን ሁለት ሆስፒታሎች አሉ። አንዱ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚተዳደር የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ቲቺንግ ሆስፒታል ሲሆን ፣ በቤንች ሼኮ ዞን የሚተዳደረው ደግሞ ሁለተኛው ነው። በተጨማሪም በዞኑ ጤና ጣቢያዎች በየወረዳውና በየክላስተሩ አሉ።

ሚዛን አማን ላይ የተሰራው እና ዩኒቨርሲቲው የሚያስተዳድረው ሆስፒታል የተገነባው በደርግ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፣ ለአርባ ሺህ ዜጎች አገልግሎት እንደሚሰጥ ታሳቢ በማድረግ ነበር። አሁን ላይ ግን ሆስፒታሉ ከአቅሙ በላይ ለሁለት ሚሊዮን ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገዷል። በዙሪያ ያሉ ዞኖች እና ክልሎች በሙሉ ሪፈራር የሚጽፉት ለዚህ ሆስፒታል ነው።

የሚዛን ሕዝብ ከ170 ሺ በላይ ነው። በመሆኑም ሚዛን ጤና ጣቢያ አንድ ጤና ጣቢያ መስጠት ካለበት አምስት እጥፍ በላይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በየወረዳው ያሉት የጤና ጣቢያ አገልግሎቶች እንዳሉ ሆኖ ሚዛን አማን ላይ ከፍተኛ ችግር አለ።

በጤና ተቋማቱ በመሠረታዊነት የመድኃኒት አቅርቦት ችግር አለ። የመድኃኒት አቅራቢ ድርጅት በሚፈለገው ልክ መድኃኒት የማቅረብ ችግር አለ። ይህ ደግሞ ከጤና መድህን ክፍያ ጋር ተያይዞ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው።

በዞኑ ውስጥ በተደረገው ግምገማ ማህበረሰቡ ማግኘት ያለበትን በተለይም በእናቶች ጤና ኤክስቴንሽን ላይ የመቀዛቀዝ ሁኔታ አለ፤ ይህን ለማስተካከል ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና ተሰጥቷል። በአዲሱ የጤና ፍኖተ ካርታ የተቀዛቀዘውን የጤና ኤክስቴንሽን ለመመለስ በንቅናቄ ሥራዎች ተከናውነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በጤና ጣቢያ ላይ ያለው ችግር የመድኃኒት አቅርቦት ብቻ ነው? የሚሰራጨውንስ በተገቢው ሁኔታ ከመጠቀም አንጻር ያለው ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** ጤና ጣቢያ ላይ የመድኃኒት አቅርቦት ችግር እንዳለ ሆኖ የቀረበውን መድኃኒትም በአግባቡ ያለመጠቀም ችግር አለ። ይህም በቀጣይ መታረም ያለበት በመሆኑ እንደአቅጣጫ ተይዞ እየተሠራ ነው። በጤና ጣቢያዎች በእርዳታ መልኩ የሚመጡና በግዥ የሚመጡ መድኃኒቶችን በአግባቡ ለኅብረተሰቡ የመስጠት ችግር አለ። አልፎ አልፎ በተወሰኑ የጤና ባለሙያዎች ዘንድ አካባቢያቸው ላይ የራሳቸው የግል ድርጅት በመክፈት መድኃኒቶችን ወደ ራሳቸው ድርጅት የመውሰድ ዝንባሌም ተስተውሏል፤ ይህንን ለማስተካከል እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ያለው የትምህርት ተደራሽነትና የትምህርት ቤቶች ደረጃ የማሻሻል ሥራ ምን ላይ ተሰርቷል?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በትምህርት ዘርፉ እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን እንደ ዞንም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው። በዞኑ በ2015 ዓ.ም በነበረው የስምንተኛ ክፍል ፈተና 10 ሺ 397 ተማሪዎች ፈተና የተቀመጡ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ 2 ሺ 22 ተማሪዎች ፈተናውን አልፈዋል። በዚህም ውጤት መሠረት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የማለፍ ሁኔታ 26 በመቶ ላይ ይገኛል። በዚህ ተመሳሳይ ዓመት የ12ኛ ክፍል 4 ሺ 190 ተማሪዎች ፈተና ተፈትነው 94 ተማሪዎች በቀጥታ ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል። ይህም ሁለት በመቶ ነው። በሪሚዲያል 342 ተጨማሪ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል።

ይህ የሚያሳየው ከፍተኛ ሥራ የሚጠይቅ መሆኑን ነው። የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅና አካባቢው ላይም ብቁና የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት ሰፊ ጥረት እያደረግን ነው። ይህን ለማሳካት በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ ልዩ ድጋፍ እያደረግን ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪና የመጽሐፍት ጥምረታውን አንድ ለአንድ አድርሰናል።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ከሕዝቡ 48 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ የወረዳ በጀትን ጨምሮ 37 ሚሊዮን ሰብስበናል። ከዚህም በ22 ሚሊዮኑ ብር መጽሐፍት ታትመው ስርጭት ተከናውኗል።

**አዲስ ዘመን፡- የዞኑን ሕዝብ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊው መስክ ተጠቃሚ ለማድረግ ከዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች ተቋማት ጋር ያለው ትስስር እንዴት ይገለጻል?**



**የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ በገበታ ለትውልድ የሚሠራው ‹‹ደንቢ ሎጅ›› ከተጠናቀቀ ቀጣናው ከፍተኛ የቱሪዝም እና የኢኮኖሚ ስበት ማዕከል ይሆናል**

**አቶ ሀብታሙ፡-** ዩኒቨርሲቲዎች ከሚቋቋሙበት ዓላማ መካከል አንዱ ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት መስጠት መቻል ነው። በዞኑ ለልማት ያለው ጸጋ እንዴት በተገቢው ሁኔታ ማልማት እንደሚቻል በጥናት ላይ የተደገፈ ሥራ በመሥራት ኅብረተሰቡን ማገዝ መቻል ነው። በዚህ ረገድ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ሚዛን ካምፓስ በተመለከተ በተደጋጋሚ ይነሳ የነበረው በቂ ምርምር ድጋፍ እየተደረገ አይደለም የሚል ነው።

በግብርና ዘርፍ ጉራ ፈርዳ ወረዳ ላይ 500 ሄክታር ለምርምር የሚሆን መሬት አለ። ይህ ቦታ ለዩኒቨርሲቲው ከተሰጠ 15 ዓመት ገደማ ይሆናል። ነገር ግን እስካሁን ምንም አይነት ልማት አለማበትም። በቦታው የሚጠበቀው በርካታ ምርምሮች ተሰርተው ማህበረሰቡን መጥቀም መቻል ነው። ነገር ግን ይህ ሊሆን ባለመቻሉ ለሌላ ድርጅት እንዲያለማው ተደርጓል። እየለማ አይደለም የሚል ሃሳብ ሲነሳ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ጣልቃ እየገባችሁ ነው የሚል ቅሬታ ስለሚነሳ የማህበረሰብ ችግር እንዲፈታ ለማድረግ ብዙም አልተቻለም።

አሁንም ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰቡን ችግር በቅንነት እንዲፈታ እንጂ ከዛ ያለፈ ምንም አይነት ፍላጎት የለንም። ከዚህ ውጪ በግብርና ላይ ‹‹ሸኮ ብሪድ›› የሚል ዝርያ ላይ ጥሩ ሥራ እየሠሩ እንደሆነ እናውቃለን።

**አዲስ ዘመን፡- የሚዛን አማን አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለዞኑ ምን አንድምታ ይኖረዋል?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** የአውሮፕላን ማረፊያው ግንባታው እየተፋጠነ ነው። ለወሰን ማስከበር ዞኑ 112 ሚሊዮን ብር ክፍያ ፈጽመዋል። የኤርፖርት አጠቃላይ የግንባታ ወሰን ማስከበር 300 ሚሊዮን ይወስዳል። ይህ ሁሉ ግንባታ እየተከናወነ ያለው በውስን የመንግሥት በጀት ላይ ማህበረሰቡን በማስተባበር ነው።

ቤንች ሸኮ ዞን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ካሉ ዞኖች ለመልማት የሚያስችል ዕምቅ ሀብት ያለው ነው። የአውሮፕላን ማረፊያው ግንባታው ሲጠናቀቅ በብዙ ዘርፎች አካባቢው ይቀየራል። እዚሁ የሚመረቱ የተለያዩ ምርቶች ወደ ማዕከል በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲደርሱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ አካባቢው እንዲመጡ እድል ይሰጣል። የሚዛን አማን አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሲጠናቀቅ ዞኑን ብሎም የክልሉን ሁለንተናዊ ገጽታ ይቀይራል።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋልና የፀጥታው ሁኔታ በተጨባጭ ምን ይመስላል?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** ከዚህ ቀደም ከቴፒ ጋር ተያይዞ ሸኮ ወረዳ፤ ደቡብ ቤንችና ጉራ ፈርዳ ወረዳዎች የፀጥታ ችግሮች ነበሩባቸው። ችግሩን ወጣቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፤ በተደራጀ መልኩ ግንዛቤ በመፍጠር ችግሩ በመፈታቱ አሁን ላይ ለፀጥታ ስጋት የሆነ አንድም ቀበሌ የለም። አሁን ላይ በዞኑ ሁሉም ከፀጥታ ስጋት ወጥቶ ልማት ውስጥ ነው። አርሶ አደሩም ሆነ ኢንቨስተሮች በሙሉ አቅማቸው ልማት ውስጥ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ህዝብን ያሳተፈ ልማት ከማከናወን አኳያ የእናንተ ዞን በተጨባጭ ምን እያደረገ ነው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** የዞኑ ሕዝብ ለልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነው። ለዚህም ሼኮ ቤንች ላይ ማህበረሰቡ በራሱ ሙሉ ወጪ የ28 ሚሊዮን ብር ድልድይ እየገነባ ነው። ሼኮ ላይ በ22 ሚሊዮን ብር፣ ደቡብ ቤንች ላይ በ28 ሚሊዮን ብር ጤና ጣቢያ እየገነባ ነው። ለስፖርቱ ዘርፍም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በ80 ሚሊዮን ብር የስታዲየም ግንባታ እያካሄደ ነው። ማህበረሰቡ የሚችለውን በሙሉ እያደረገ ነው።

የሚቀሩ ነገሮች እንደተጠበቁ ሆኖ አርሶ አደሩ ቡና በኪሎ እንዲያወጣ በማድረግ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ሼኮ ላይ 30 ሚሊዮን ተሰብስቧል። ቅድም ያልናቸው የመጽሐፍ ህትመት ወጪዎችን ከማህበረሰቡ በተሰበሰበ ገንዘብ ነው የተሰራው። በልማቱ ኅብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

በተለይ ከአውሮፕላን ማረፊያ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማድረግ ያለብንን ግንኙነት እና ንግግር እያደረግን ነው። ለአውሮፕላን ማረፊያ ልማቱ ከፍተኛ ፍላጎት ስላለን ከፍተኛ ትኩረት ወስደን እየሰራን ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩንም በዚህ አጋጣሚ በዞኑ ሕዝብ ስም ማመስገን እንወዳለን። ምክንያቱም መሰረተ ድንጋይ ከማስቀመጥ ጀምሮ ሥራውም ትኩረት አግኝቶ በዚህ ልክ እና ፍጥነት እንድንሰራ ያስቻሉን እርሳቸው ናቸው።

የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ በገበታ ለትውልድ የሚሠራው ‹‹ደንቢ ሎጅ›› ከተጠናቀቀ ቀጣናው ከፍተኛ የቱሪዝም እና የኢኮኖሚ ስበት ማዕከል ይሆናል። ስለዚህ እኛ የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን የአውሮፕላን ማረፊያውን እና ሎጁን እናስጨርሳለን።

አሁን ላይ ዞኑ አቅሙ የሚፈቅደውን ሁሉ ቢሄድም የተለያዩ ፈተናዎች እያጋጠሙት ነው። የአውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክቱን የገንዘብ ሚኒስቴር እና ፕላን ሚኒስቴር ድጋፎች እንዲያደርጉልን እንፈልጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ዞኑ ለቱሪዝም ምቹ ከመሆኑ አንጻር የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በዞኑ ከፍተኛ የቱሪዝም እምቅ ሀብት አለ። ወደ ደንቢ ሀይቅ ፣ በበቃ ፣ ሸካ እና ደቡብ ቤንች ብትሄዱ ተፈጥሮን ምንም ሳይነካ እና ሳይበረዝ ታገኙታላችሁ። ሌሎች ዓለማት ላይ ተፈጥሯዊ ነገሮችን ፈልጎ ማግኘት ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። በመሆኑም ዞኑ ለቱሪዝም በጣም ምቹ ነው። ግን በፀጥታ ምክንያት ቀድሞ የነበረው የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ተቀዛቅዘው ነበር። አሁን ላይ የአካባቢው ሰላም ወደነበረበት በመመለሱ ቱሪስቶች መጥተው እንዲጎበኙ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወንን ነው።

ክብር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በልዩነት ‹‹የደንቢን ሎጅ›› ፕሮጀክት ያስጀመሩት ዞኑ ባለው የቱሪዘም ሀብት በመደመማቸው ነው። ይሁንና አሁንም ዞኑ ካለው እምቅ ሀብት አንጻር የቱሪዝም ቦታዎችን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ክፍተት አለ። በተለይ ባህል እና ቱሪዝም ላይ ከፍተኛ የማስተዋወቅ ክፍተት አለ የሚለውን በግምገማ ለይተናል።

በቀጣይ በእርግጠኝነት በቱሪዝም ዘርፉ በርካታ ገቢ የሚያስገኙ ለዞኑ ብሎም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚደግፍ ሥራዎችን እናከናውናለን። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሚዛን ወዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ መጠየቁ ቀርቶ ሚዛንን ካለየሁ የሚልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

**አዲስ ዘመን ፡- የአሁኑ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀደም ብሎ በደቡብብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሥር በነበረበት ጊዜ ፍትሐዊ የልማት ተጠቃሚ አልነበረም የሚሉ አሉ። እዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው ?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** ፍትሐዊ የልማት ተጠቃሚ አልነበረም በሚለው ላይ ምንም አከራካሪ አይደለም። በእርግጥ የደቡብ ብሔር ፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በነበርንበት ጊዜ መልካም ነገሮችም ነበሩ። ብሔር ብሔረሰቦች በመተሳሰብ የኖሩበት ሂደቶች ጥሩ ነበር። ይሁን እንጂ ከፍትሐዊ ተጠቀሚነት አንጻር ቅሬታዎች ነበሩ።

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከማዕከላዊ መንግሥቱ እና ከበፊቱ የክልል መቀመጫ ሀዋሳም ሩቅ ነው። በመሆኑም ቀደም ብሎ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ የሚረዳ አካል ነበር የሚል እምነት የለንም። ይህ በትክክል የታዘብነው ነው። በደቡብ ብሔር ፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በነበርንበት ወቅት ከአካባቢያችን የተመረጡ በክልሉ በከፍተኛ ደረጃ የመንግሥት ኃላፊነት የተቀበሉ ሰዎች ቢኖሩ ኖሮ ዞኑ ወይም ኅብረተሰቡ ምን ይፈልጋል የሚለውን ይረዱ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ ይህ ስላልነበር የክልሉ አመራሮች ኅብረተሰቡ ምን እንደሚያስፈልገው አያውቁም ነበር። በዚህም የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ አካባቢ ከልማት ተጠቃሚነት እርቆ ቆይቷል።

በወቅቱ አመራር ስለነበርኩ አብዛኛውን ነገር አውቀዋለሁ። ለግማሽ ቀን ስብሰባ ሁለት ቀን ተጉዘን ሀዋሳ እንሄድ ነበር። ሁለት ቀን ጉዞ ያደረክበት ስብሰባ ሶስት ሰዓት ተጀምሮ አምስት ሰዓት ላይ አልቋል ሊባል ይችላል። በዚህም አካባቢው ከፍተኛ የሆነ የሀብት ፣ጉልበት እና ጊዜ ብክነት በተደጋጋሚ ያጋጥመው ነበር። በዚህ የተነሳ በወቅቱ የማህበረሰቡን ጥያቄ የሚሰማ እና የሚፈታ እንዲሁም የሚረዳ መዋቅር እና አደራጃጀትም አልነበረም። አሁን ላይ እነዚህ የኅብረተሰቡ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል። ይህ ደግሞ ለሕዝባችን ታሪካዊ ምላሽ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በአዲስ ክልል ውስጥ እንደመገኘታችሁ ዞኑን ብሎም ክልሉን ለማስተዳደር አዲስ መመሪያዎች መቅረጽን ይጠይቃል። ከዚህ አንጻር የሚፈጠሩ ክፍቶችን እንዴት እየፈታችሁ ነው?**

**አቶ ሀብታሙ፡-** በአዲሱ ክልል በርካታ እየተሻሻሉ ያሉ መመሪያዎች፣ ሕጎች እና ደንቦች አሉ። በሂደት ላይ ያሉም አሉ። ከሠራተኛ ጋር ተያይዞ የመዋቅር ሪፎርም ተድርጓል። አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ የገጠር መሬት ግብርና የተመለከተ ማሻሻያ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ሀብታሙ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ነፃ ሃሳብ

# የከተማዋ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ነገር "የላጭን ልጅ ..." እንዲሉ

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን ወደ ጎን መስፋፋትና ሽቅብ መወርወር ታሳቢ በማድረግ የንጹህ የመጠጥ ውሃ ፍላጎቷ ለመመለስ ይሰራል:: ለእዚህም የግድቦቹን አቅም በማሳደግ፣ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን በመቆፈር መውተርተሩን ተያይዞታል:: በእነዚህ የውሃ አማራጮቹ የሚያገኘውን ንጽህ ውሃም ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ እየሰራ ይገኛል::

የከተማዋ ውሃ ፍሳሽ ባለስልጣን የውሃ ልማቱን አጠናክሮ መቀጠል እንዲያስችል ተቋማት የራሳቸውን ውሃ ከጥልቅ ውሃ ጉድጓድ እንዲያመርቱ የሚያስችል ሌላ አማራጭ እየተከተለም ነው:: ጥሩ ስራ ነው:: በዚህ አማራጭ ከተማ አስተዳደሩ የሚያመርተውን ውሃ በከፍተኛ ደረጃ ይሻሙ የነበሩ ተቋማት ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ችሏል::

አንድ ተቋም በራሱ ውሃ አገኘ ማለት ከከተማዋ ውሃ አቅርቦት ያገኘው የነበረው ውሃ ለበርካታ መኖሪያ ቤቶች የሚውልበትን ምቹ ሁኔታም ይፈጥራል:: ተቋማቱ በችግር ጊዜ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊታደጉ የሚችሉበት እንዲሁም ለከተማዋ ውሃ አገልግሎት ውሃ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ውስጥም ሊገቡ ይችላሉና በመልካም ተግባር ሊታይ የሚገባው ነው::

ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ሁሉ መንገድ በንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ረገድ ብዙ እየሰራ ቢሆንም፣ የውሃ ፍላጎትና አቅርቦቱ ክፍተት ከፍተኛ መሆኑ ቀጥሏል:: የችግሩን ደረጃ ለማሳየት ጥናት ማድረግም የተካሄደ ጥናት መጥቀስም የሚያስፈልግ ባይሆንም፣ ከከተማዋ ጥቂት ወረዳዎች በስተቀር አብዛኞቹ በሳምንት አንዴና ሁለቴ የሚያገኙ መሆናቸውን የባለስልጣኑ መረጃዎችም ይጠቁማሉ:: ይህ ክፍተት በራሱ የፍላጎቱን እየጨመረ መምጣት ያመለክታል::

ከዚህም በጠበቡ ቀናት የሚያገኙ ወረዳዎች እንዳሉም ይገለጻል:: የውሃ ፈረቃ ካልነበረበት፣ ወደ ፈረቃ የተገባበት እንዲሁም የውሃ ፈረቃው ሰፊ ከነበረበት ወደ ጠባቡ እየገባ ያለበት ሁኔታም እጥረቱን ቁልጭ አድርገው ያመለክታሉ:: የህዝብ ቁጥሩ እየጨመረ እንዲሁም ውሃ በስፋት የሚፈልግ አኗኗር እየተስፋፋ መምጣት ፣ የሆቴሎች ፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ወዘተ መስፋፋት የውሃ ፍላጎቱ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታሉ::

በከተማዋ የተለያዩ መንደሮች በጀሪካን ውሃ የሚያቀርቡ በርካታ ጋሪዎች የሚታዩ መሆናቸው፣ በቦቴና በሌሎች የተለያዩ አማራጮች/በአይሱዙ/ ውሃ በስፋት ለነዋሪዎች እየቀረበ ያለበት ሁኔታም እንዲሁ የውሃ እጥረቱ ማሳያዎች ናቸው:: አብዛኞቹ የከተማ ነዋሪዎች / በተለይ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር የሌላቸው ቤቶች/ በተቀመጠላቸው ፈረቃ መሰረት ውሃ ከሄደበት ቀን አንስቶ እስከሚመለስ ድረስ ያሉትን ቀናት በሙሉ መጠቀም የሚያስችለውን ውሃ በበርሜሎች፣ ጀሪካኖች፣ ወዘተ ሁሉ በመያዝ ከተቀዱ በርካታ አመታት ተቆጥረዋል::

ይህን አለማድረግ ማለት አይደለም ትንሽ እንኳ ሳያደርጉ መገኘት የሚያስከትለውን ችግር ነዋሪው በሚገባ ስለሚያውቅ ቆሞ ያድራታል፤ ይውላታል እንጂ ውሃ መጠራቀም እንዳለበት አምኖ ውሃ ማጠራቀምን የህይወቱ የስራ አካል አርጎ ይዞታል:: የቤቱን የበረንዳውን የግቢውን ጥቂት የማይባል ቦታ የያዙት የውሃ ማጠራቀሚያ ቁሶች ናቸው:: ይህን ካላደረገ ለውሃ አገልግሎት በወር ሊከፍል ከሚችለው ገንዘብ በላይ ለአንድ ጀሪካን ውሃ መግዣ ሊያወጣ ይችላል:: ይህ እንዲሆን አይፈቅደም::

በአንድ ወቅት በእዚሁ ጋዜጣ ላይ አንድ ጋዜጠኛ የውሃ አቅርቦትን አስመልክቶ በጻፈው መጣጥፍ እኛ ቤት ውሃ እንዲቀበሉ፣እንዲያስተላልፉ የተገጠሙ ቁሶች ሁሉ ውሃ ጠምቷቸው ነው የሚሰነብቱት ያለው ታወሰኝ:: ፊት መታጠብ በጆግ፣ ገላ መታጠብ በባልዲ፣ መጸዳጃ ቤት ውሃ የሚለቀቀውም እንዲሁ በባልዲ ነው:: ወደ ማብሰያ ክፍል ሲገባም ያው ነው፤ ውሃ በባልዲና በጆግ ነው የሚንሸራሸረው:: ቁሶቹ በራሳቸው ውሃ ይዘው፣ የሚለቁትና የሚለቀቅባቸው በሳምንት አንዴና ሁለቴ ሆኗል:: እንደ ጠማቸው ይከርማሉ::

በሰለጠነ ዓለም ዘይቤ የተሰሩ የመጸዳጃ እና ማብሰያ ቤቶች ታንከር ከሌለ በስተቀር በሳምንት ከሁለት ቀናት በላይ በወጉ የሚጠቀምባቸው የለም፤ ምክንያቱ የውሃ እጥረት ነው:: በዚህ ላይ የውሃ ቁጠባው አለ:: እዚህ ከተማ ውስጥ ውሃ አይቆጠብም የሚሉ ሰዎች አንዱን ጎን ብቻ የተመለከቱ ናቸው፤ ለመኪና ማጠቢያ መዋሉ፣ ቧንቧ ስብራት ሲገጥመው ቶሎ ካለመጠገኑ ጋር በተያያዘ ውሃ በከንቱ እየፈሰሰ ያለበት ሁኔታ ታይቶ ነው አይቆጠብም የሚባለው::

> ስለውሃ እንነጋገር ከተባለ ማድረግ የሚሻለው እንዴት ተደርጎ ውሃ ይልማ ለሚለው ጥያቄ አንዱ መልስ ተበድሮም ተለቅቶም ጨክኖ ልማቱን ማካሄድ ነው

እኔ ግን ካለው ችግር አኳያ አዲስ አበባ ውሃ በደንብ የሚቆጠብባት ከተማ መሆኗን አስረግጬ እናገራለሁ:: እኛ ውሃ በፈረቃ የምናገኝ ወገኖች ውሃ ቆጣቢዎች ነን:: በስንት መከራ በበርሜል በጀሪካንና በመሳሰለው ያጠራቀመውን ውሃ የሚያባክን ሞኝ የለም:: እንዳውም ችግሩ የውሃ ቁጠባን አስተምሯል ባይ ነኝ:: የእቃ እጣቢ አጠራቅሞ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት የሚያውል ጥቂት የሚባል አይደለም:: አለበለዚያ የመጸዳጃ ቤት መጥፎ ጠረን ጣጣ ይከተላል::

ከከተማዋ ወረዳዎች በጣም ጥቂት ከሚሆኑት በስተቀር አብዛኞቹ በሳምንት አንዴና ሁለቴ የሚያገኙትን ውሃ ያባክናሉ ብሎ ማለት አያስኬድም:: በመሰረቱ በከተማዋ ከተፈጠረውና በቀጣይም ይፈጠራል በሚል ከተሰጋበት የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት አኳያ ሲታይ አሁን መነጋገር ያለብን በስፋት መልማትና ለከተማ መቅረብ ስላለበት ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንጂ ስለውሃ ቁጠባ ነው ብዬ አላምንም::

ስለውሃ ቁጠባ ማውራት ተገቢ አይደለም እያልኩ አይደለም:: በመሰረቱ ውሃ በተጠማ ከተማ ውስጥ የውሃ ብክነት እንዲኖር ማድረግ ትክክል አይደለም:: ውሃ መቆጠብ ነው የሚያዋጣው:: በውሃ እጥረት ውስጥ ለሚገኝ ማህበረሰብ ስለውሃ ቁጠባ መንገር ለቀባሪው አረዱትም ይሆናል:: ውሃ ሲገኝ እኮ ነው የሚባክነው:: ውሃ በአሳር በሚገኝበት ሁኔታ በተለያዩ የውሃ ማከማቻዎች ውሃ ያጠራቀመ ሰው ውሃ እንዲባክን ያደርጋል ማለት ብዙም አያስኬድም::

በአዲስ አበባ ከተማ የውሃ ልማቱን በስፋት ማካሄድ የግድ የሚል ሌላም አብይ ጉዳይ አለን:: ከተማዋ የሀገሪቱ ዋና ከተማ፤ በሌሎች የሀገሪቱ ሞዴል ሆና የምትታይ ከተማ ፣የአፍሪካም የዓለም አቀፍ ተቋማትም መቀመጫም እንደመሆኗ፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ ጉዳይ አንገብጋቢ አጀንዳ ነው:: የፌዴራል መንግሥቱም ሆነ የከተማ አስተዳደሩ ከተማዋ እንድትደርስ ከሚጠበቅባት ስፍራም ሲታሰብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ልማቱም ጉዳይ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል::

አዲስ አበባን ለምታህል የሀገሪቱ ዋና ከተማ፣ የአህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ከተማ አሁን ውሃ እየለማና እየቀረበ ያለበት መንገድ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: ከመውተርተር የዘለለ አይሆንም:: የከተማ አስተዳደሩ የውሃ ፍላጎቱን ለመመለስ የሚያስችል ወሳኝ የውሃ ልማት ሥራ ውስጥ እየገባ አይደለም::

የችግሩ ስፋት የንጹህ መጠጥ ውሃ ልማቱ ከእስከ አሁንም በእጅጉ የሰፋ ሥራ ውስጥ መግባትን የግድ ይላል:: ከአመታት በፊት አንድ ግዙፍ ግድብ/ ሲቢሉ ነው የሚባለው/ ለመገንባት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ወሬውም የለም:: ያንን ግዙፍ ለመገንባት አቅሙም ሁኔታውም ቢፈቅድ፣ በሆነ መልኩ ውሃ ያስገኛል ተብሎ ወደ ግንባታ መገባት ያለበት አይመስለኝም::

የከተማዋ የውሃ ፍላጎት በእጅጉ እየጨመረ መምጣት፣ ከተማዋን እንደ ስሟ የማድረግ፣ ከአህጉሪቱ ትላልቅ ከተሞች ተርታ የማሰለፍ ራእይ ለከተማ የደም ያህል የሚቆጠረውን ውሃ ለማልማቱ ሥራ ቅድሚያ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፤ ለእዚህም ምንም እንኳ በዘርፉ ባለሙያ ባልሆንም ቀደም ሲል የተካሄዱ ጥናቶች በቅድሚያ መከለስ ይኖርባቸዋል እላለሁ::

ምን ያህል ውሃ ለማግኘት፣ መቼ ለማግኘት ፣ ምን ያህል ወጪ በማድረግ የሚሉትን የሚመለስ ጥናት በድጋሚ መስራት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ:: ሌላ አዲስ ግድብ የመገንባት ወይም ነባሮቹን በወሳኝ መልኩ የማስፋፋት ጉዳይም ብዙም ሲወራላቸው አይሰማምና ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ሊደርስ ይችላል ብሎ መገመት አይከብድም::

አሁን በዋናነት የተያዘው ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን መቆፈር ነው:: ይህ ሀገሪቱ በከርሰ ምድር ውስጥ ያላትን የውሃ ሀብት ለመጠቀም እያደረገች ያለችው ጥረት ጥሩ ሆኖ ሳለ ከቅርብ ጊዜ የሚወጡ መረጃዎች ይህም የራሱ ችግሮች እንዳሉበት እየጠቆሙ ናቸው::

የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁጥር በጨመረ ቁጥር ሊገኝ የሚችለው የውሃ መጠን እየቀነሰ ይመጣል የሚል መረጃ በዘርፉ ባለሙያዎች እየተጠቆመ ነው:: በአንድ አካባቢ ብዙ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ሲቆፈሩም ምንጩ አንድ ነውና የሚጠበቀውን ማግኘት ሊያዳግት ይችላል:: በቂ ውሃ ለማግኘት በጣም ብዙ ርቀት መቆፈር የግድ እየሆነም ነው::

ይህን ቁፋሮ ማድረግ የሚችሉ ማሽነሪዎችን በማግኘት በኩል ተግዳሮት እንዳለ የሚናገሩ ወገኖች አሉ:: አሁን ባለው የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ የከርሰ ምድር ውሃ ሊሟጠጥ እንደሚችልም የዘርፉ ባለሙያዎች እያስገነዘቡ ናቸው:: ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ልማቱ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መካሄድ እንዳለበት ነው::

የከተማዋ ንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር መሰረታዊ ነው:: ስለዚህ መሰረታዊ ችግር ማውራት ውስጥ በስፋት መግባት ያስፈልጋል:: ስለውሃ እንነጋገር ከተባለ ማድረግ የሚሻለው እንዴት ተደርጎ ውሃ ይልማ ለሚለው ጥያቄ አንዱ መልስ ተበድሮም ተለቅቶም ጨክኖ ልማቱን ማካሄድ ነው:: ልማቱን ለማካሄድ ደግሞ አሁን ያሉት የልማት አማራጮች ብቻቸውን በቂ አይደሉም::

ከግድብ አኳያ ሲታይ ዱሮም የምናውቃቸው ግድቦች ናቸው አገልግሎት እየሰጡ ያሉት፤ እርግጥ ነው እቅማቸውን የማሳደግ ሥራ ተሰርቶላቸዋል:: በርካታ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ተቆፈረው ወደ ሥራ ገብተዋል:: ይሄ ሁሉ በቂ ስላለመሆኑ በከተማ ያለው የውሃ እጥረት ያመለክታል::

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት መንግሥት ከዘርፉ ባለሙያዎች ሰፊ ምክክር ማድረግ ይኖርበታል:: ባለሙያዎቹ በተለያዩ መድረኮችና የተለያዩ አማራጮች ላይ ሃሳባቸው እያንሸራሸሩ ናቸው:: ሌሎች ግዙፍ ግድቦችን ከአዲስ አበባ ዙሪያ ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች ድረስ በመዝለቅም ቢሆን ገንብቶ ስለመጠቀም ማሰብ ውስጥ መግባት ሲሉ አስተያየት የሚሰጡ ባለሙያዎች አሉ:: የጥልቅ ውሃ ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን በመጠቆም ሌሎች የውሃ ማግኛ አማራጮችን ማሰብ ይገባል ሲሉ አስተያየት የሚሰነዘሩም ይደመጣሉ::

ከዚህ በኋላ የሚካሄዱ ለተለያዩ የመሰረተ ልማትና የመሳሰሉት ሥራዎች የሚካሄዱ የግድብ ልማቶች የንጹህ መጠጥ ውሃን ታሳቢ ማድረግ እንዲችሉ ከወዲሁ ታስቦ ተደርጎ ሊሰራ ይገባል ሲሉ ሰሞኑን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተካሄደ የኮንትስትራክሽን ኢንዱስትሪ መድረክ ላይ የጠቆሙም ባለሙያዎች ነበሩ:: ይህም ለኤሌክትሪክ ፣ ለመስኖና ለመሳሰሉት ልማቶች የሚገነቡ ግድቦች ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚውሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት የሚል አንድምታ አለውና ይጠቅማል::

ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያላት ፣ የገጸ ምድር እንዲሁም የከርሰ ምድር ውሃ ሀብቷ ከፍተኛ የሆነች፣ በአጠቃላይ የውሃ ማማ የምትባል ሀገር ዋና ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ የላጭን ልጅ ቅማል በላው እንዲሉ በንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር መጠቀስ አልነበረባትም:: የዘርፉ ባለሙያዎች አሁን ስለተፈጠረው የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር ብቻ አይደለም የሚናገሩት:: በቀጣይ ስላለው ስጋትም ነው እየጠቆሙ ያሉት:: ይህን አዳምጦ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ከወዲሁ መስራት ያስፈልጋል::

የንጹህ መጠጥ ውሃ ጉዳይ ለአዲስ አበባ ከተማ አጀንዳ ተደርጎ መያዝ አለበት:: የሀገሪቱ ዋና ከተማ፣ የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ከተማ የውሃ ማማ የምትባል ሀገር ዋና ከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት ዜና የሚሰራበትም የሚሰማባትም መሆን የለባትም::

የአህጉር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ሀገሮች ከተሞች፣ ያደጉትና በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ከተሞች ንጹህ የመጠጥ ውሃ በማልማትና በማቅረብ በኩል የሄዱባቸውን መንገዶች አጥንቶ አቅም የሚፈቅደውን መተግበር መጀመርም ያስፈልጋል:: የውቅያኖስና ባህር ውሃ የጨው መጠንን እያመከኑ፣ ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን እያከሙ፣ ወዘተ የውሃ አቅርቦታቸውን የሚያሳድጉ ሀገሮች ጥቂት አይደሉም፤ እኛ ይህን ሁሉ ማድረግ ውስጥ የሚያስገባ ሁኔታ ባይኖረንም፣ ሀይቆቻችንን ግድቦቻችንን ትላልቅ ወንዞቻችን ላይ መስራት ስለመጀመር ቢያንስ ማሰብ ግን ያለብን ይመስለኛል::

ከተማዋን ከአፍሪካ ታላላቅ ከተሞች ተርታ ለማሰለፍ እንዲሁም እንደ ስሟ ለማድረግ ግዙፍ የኮሪደር ልማት እየተከናወነ ነው:: ለዚህ አላማ ለምትገነባው አዲስ አበባ የሚሆነውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ለማልማትና ለነዋሪዎቿ፣ ለተቋሞቿ፣ ወዘተ ለማቅረብ ሥራው በፍጥነት መጀመር አለበት:: ዝግጅቱን አስቀድሞ በማድረግ ልክ እንደ ኮሪደር ልማቱ ግንባታው በርብርብ የሚፈጸምበትን ሁኔታ መፈልግ ይገባል::

ይህ ሥራ መጀመር ከነበረበት ጊዜ በእጅጉ ዘግይቷል:: ይህን ሊያካክስ የሚችል ሥራ በመሥራት የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረትን የከተማ መገለጫ ከመሆን መውጣት ብቻ ሳይሆን በቂና ዘላቂ አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ የከተማዋ ውበት መገለጫ እንዲሆን ማድረግ ይገባል:: ይህ ሲሆን የላጭን ልጅ ምን በላው የተባለው አባባል ሀገሪቱንም ከተማዋንም የማይገልጻቸው ይሆናል::

# ለአምራቾች የገበያ ትስስርን የፈጠረው ኤክስፖ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

‹‹ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ›› የሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠረ ይገኛል። ንቅናቄው ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የሀገር ውስጥ ምርቶች የገበያ ተደራሽነታቸው እየሰፋ መምጣቱ ይነገራል። ንቅናቄ በተለያዩ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን፤ በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሚሊኒየም አዳራሽ የከፈቱት ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከግንቦት 1 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ግንቦት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ሲካሄድ መቆየቱ ይታወሳል።

በኤክስፖ የማጠቃለያ መርሀ ግብር ላይ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ከ210 በላይ ኩባንያዎች ምርታቸውን አቅርበው ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ተከናውኗል። በ74 የገበያ ትስስር መፈጠሩንና ሰባት የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያን ምርት ለመግዛት መስማማታቸውን ገልጸዋል።

ኤክስፖ ላይ የተሳተፉ አምራቾችም ኤክስፖው በፈጠረላቸው የገበያ ትስስር ምርቶቻቸውን እንዲያስፋፉ ምቹ ሁኔታዎች እንደተፈጠረላቸው ይገልጻሉ። አቶ አከመል ሽኩር ‹‹የአውሳን››ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሊቀመንበር ናቸው። ‹‹አውሳን›› ዓለም ገና ወለቴ አካባቢ ባለ ኢንዱስትሪ ዞን የተመሠረተ ጨርቃጨርቃና አልባሳትን የማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ነው። 30 ሠራተኞች ይዞ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ አሁን ላይ ከ300 በላይ ሠራተኞች እንዳሉት አቶ አከመል ይናገራሉ።

ድርጅቱ ከሕፃናት ጀምሮ እስከ አዋቂ እድሜ ክልል ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚሆኑ አልባሳት የሚያመርት ሲሆን፤ ሱሪዎች ፣ ሸሚዞች ፣ጃኬቶችን እና የመሳሰሉ የተለያዩ አልባሳትን ያመርታል። በተለይም ደግሞ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የደንብ ልብሶች (ዩኒፎርሞችን) ያመርታል። ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎችን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርሞችን) አምርቶ ማቅረቡንም አስታውሰዋል።

ያመረተቻቸውን የደንብ ልብሶች ተማሪዎች ለብሰው ሲያዩአቸው በእጅጉ እንደሚደሰቱ ነው አቶ አከመል የሚገልጹት። በአሁኑ ጊዜ ሀገር ውስጥ ተመርተው የሚለበሱ ልብሶች እየተበራከቱ በመሆናቸው በዚያው ልክ ደግሞ ለባሾችም እየበዙ መምጣት የሀገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታቱ በመሆናቸው ያለውን የገበያ እንቅስቃሴ የተሻለ እንዲሆን አድርጎታል ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹ስራውን ስንጀምር አብዛኛው ሰው የሀገር ውስጥ ምርቶች ጥራትና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው በሚል አይጠየቅም ነበር፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን የኅብረተሰቡም አመለካከት እየተቀየረ በመምጣቱና እኛም ደግሞ እያደረ በጥራት ላይ ማሻሻያዎች በማድረጋችን አሁን ላይ የእኛን ምርቶች የሚመለከቱት ሰዎች፤ እነዚህ አልባሳት እውን ሀገር ውስጥ የተመረቱ ናቸው የሚል ጥያቄን እንዲያነሱ አድርጓል›› ይላሉ።

ድርጅቱ ከስፌት ጀምሮ በጥራት እየተሻሻለ መምጣቱ፤ የሰውን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ጥራታቸውን የጠበቁ አልባሳት እያመረተ ነው የሚሉት አቶ አከመል፤ የምናመርተው አልባሳት ከውጭ ከሚገቡት የበለጠ ጥራት ያላቸው በመሆናቸው ብዙ ሰው እየለበሳቸው እየተጠቀመባቸው ይገኛል ሲሉም ያስረዳሉ።

አቶ አከመል ለአልባሳት የሚሆኑ የጥሬ እቃ አቅርቦት ከሀገር ውስጥና ከውጭ እንደሚያስገቡ ይገልጻሉ። ከውጭ የሚገቡ ጥሬ እቃዎች ለማምጣት ያለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ፈተና እየሆነባቸው መሆኑን አንስተው፤ ችግሮቹ የሚቀረፍ ከሆነ የተሻለ ምርቶች ማምረት እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ላይ ያለው የፋብሪካው የማምረት አቅም እንደሚመረተው የጨርቅ አይነት የሚወሰን ቢሆንም በቀን በአማካይ ከ3ሺ እስከ 5ሺ አልባሳት ይመረታል። ምርቶቹን መርካቶ ለሚገኙ አከፋፋዮች ያስረክባሉ። እንዲሁም ምርቱን ለሚፈልጉ ተቋማት ያስረክባሉ።

እነዚህም ምርቶች ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ ባሻገር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንዲቻል ያሉ ሂደቶችን በማጠናቀቅ በቅርቡ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑንም ገልጸዋል። የሀገር ውስጥ አልባሳት በዋጋ ደረጃ ቢሆን የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ባማከለ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአከፋፋዮች የሚያስረክቡ መሆኑን ነው አቶ አከመል ያስረዱት፤

የጨርቃጨርቅ ሥራ ዘርፉ በአብዛኛው የሰው ኃይል የሚይዝ መሆኑና በዘርፉ የሚሰማሩ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ ሴቶች ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሥራ የመልቀቅ ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቅሶ፤ በእነዚህ ሰዎችን ለመተካት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

‹‹ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ላይ ተሳታፊ መሆናችን ብዙ ሰዎች እንድንገናኝና የገበያ ትስስር እንድንፈጥር ረድቶናል። የመጀመሪያው ምርታችንን ተመልክተው እንደዚህ አይነት አልበሳት ሀገር ውስጥ መመረታቸውን ማወቃቸው በራሱ ትልቅ ግብዓት ነው። ሁለተኛው የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል እድልን የፈጠረ ነው። በተጨማሪም ለእኛም ከሌሎች ጨርቅ አምራቾች ጋር ስምምነት ለመፍጠር የሚያስችል እድል ፈጥሮልናል›› ይላሉ።

ሌላኛው የኤክስፖ ተሳታፊ የንብ ከረሜላ ፋብሪካ የማርኬቲንግ ማናጀር አቶ ፋሲል ናደው ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ፋብሪካው የሚገኘው ቡራዩ ታጠቅ አካባቢ ኢንዱስትሪ መንደር ውስጥ ነው። የንብ ከረሜላ ፋብሪካ ከ50 ዓመት በላይ ያስቆጠረ አንጋፋ ድርጅት ነው። በመጀመሪያ ላይ በከረሜላ ምርቶቹ ነበር የሚታወቀው። አሁን ላይ ወደ ቸኮሌት ምርት ገብቶ የተለያዩ ቸኮሌቶችን እያመረተ ለገበያ እያቀረበ ይገኛል።

ለቸኮሌት ምርት የሚውሉ ጥሬ ግብዓቶችን በብዛት የሚያስመጡት ከምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች ከጋና እና አይቬሪኮስት ሲሆን፤ የሚመጣው የግብዓት አይነት የኮካዋ ፍሬ ነው። የኮካዋ ፍሬ በፋብሪካ ውስጥ በተለያየ ሥርዓት ተቀነባብሮ የሚጣፍጥ ሆኖ ለገበያ ያቀርባል።

በአሁኑ ሰዓት ምርቶቹ በሱፐር ማርኬቶች፣ በሆቴሎች፣ በሱቆች ስለሚገኙ በጣም በርካታ ደንበኞች ምርቶቻችን ይጠቀማሉ የሚሉት አቶ ፋሲል፤ ‹‹ምርቶቹ በገበያው በደንብ የሚታወቁ ከመሆናቸው በላይ ሀገር ውስጥ የትኛው ቦታ ላይ ቸኮሌት ሲባል የንብ ቸኮሌት ታዋቂና ተመራጭ ነው›› ይላሉ። ንብ ቸኮሌት ያገኘውን ይህን የታዋቂነትና ተመራጭ በደንብ ሰርጾ ገብቶ ‹ብራንድ እንዲሆን› ለማድረግ አሁንም የማስተዋወቅ ሥራዎች እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል።

‹‹የንብ ቸኮሌት በሀገር ውስጥ ታዋቂም ከመሆኑም በላይ በዋጋው ቢሆን ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለገበያ እየቀረበ ነው፤ ቸኮሌቱ የራሳችን የሆነ ጣዕምና ጥራት አለው››የሚሉት ፋሲል፤ ደንበኞችም ይህን በሚገባ ስለሚያውቁ ምርቶቻቸውን እንደሚወዱት ይናገራሉ። አሁን ላይ በሀገሪቱ የቸኮሌት ገበያ ተቆጣጠሪ ቢኖርም ከውጭ የሚገባውን ለማስቀረት የሚያስችል ሥራዎች እየሰሩ መሆኑን ይገልጻል። ለዚህ የሃምሳ ዓመታት ልምድ በመጠቀም የሚያስፈልገው የማምረት አቅም እና ጥራት በመጨመር ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

አቶ ፋሲል ‹‹በኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ የገበያ ትስስር በመፍጠር በርካታ ደንበኞች ምርቶቻችንን እየገዙ እየተጠቀሙ ነው፤ ደንበኞች ምርቱን ከተጠቀሙ በኋላ የሚሰጡት አስተያየት ደስተኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው›› ይላሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ከድርጅቱ ሱቆችም ሆነ ኪዮስኮች፣ ሱፐር ማርኬቶች እና ሃይፐር ማርኬቶች ንብ ከረሜላና ቸኮሌቶቻችንን ይወስዳሉ። ድርጅቱ ኬክ ግብዓቶችንም ስለሚያመርት፤ ለሆቴሎች፣ ለካፌዎች ብስኩትና ብስኩት መሰል ነገሮች ለሚያመርቱ እንዲሁም ኮርንፊሌክስ እና አይስክሬም ለማምረት በግብዓትነት የሚጠቀሙ ድርጅቶች ደንበኞቹ ናቸው። አሁን ላይ ያለው የገበያ ፍላጎት ሰፊ ስለሆነ የማምረት አቅምን በመጨመር ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ነው።

ድርጅቱ በቋሚ ሠራተኞች ከ400 በላይ ያሉት ሲሆኑ፤ ለበርካታ ሠራተኞች የሥራ እድል የፈጠረ ነው። ድርጅቱ የቤተሰብ ድርጅት ሲሆን የመጀመሪያ ትውልድ ከረሜላውን ሲሰራ ሁለተኛው ትውልድ ደግሞ ወደ ቸኮሌት አድርሶታል። ወደፊት ብዙ ሥራዎችን እየሰራ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚሄድ ይሆናል ሲሉ አስታውቀዋል።

ድርጅቱ ዋነኛ ተግዳሮት የሆነበት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲሆን፤ ይህን መሻገር ከተቻለ የተሻለ ሥራን መስራት የሚችል መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ላይም ከመንግሥትም ብዙ ድጋፎች እያገኙ መሆኑንም አንስተዋል።

በቀጣይ በሀገር ውስጥ የሚመረተው የቸኮሌት ምርት ለውጭ ገበያ የመላክ በእቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህ ዓመት መጨረሻ ቢያንስ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ የመላክ እቅድ ይዘው ለዚህ በዝግጅቱ ሂደት እንደሚገኙ አመላክተዋል።

ሌላው የኤክስፖው ተሳታፊ የሆነው ኤርጌንዶ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን፤ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳምሶን ተሰማ በበኩላቸው ኤርጌንዶ ከተመሰረተ ከ24 ዓመት በላይ ማስቆጠሩን ይገልጻሉ። በመጀመሪያ ላይ ሥራ ሲጀመር በሀገሪቱ ብራንድ ሆነውን ኤርጌንዶ ጫማ ሲያመርት እንደነበር አስታወሰዋል። ረጅም ጊዜ በጫማ ሥራ ላይ ከቆየ በኋላ አሁን ላይ ለተለያዩ ጂሞች፣ ለሕፃናት መዋያዎች፣ ለሕፃናት መጫወቻ እና ለተለያዩ ግብዓት የሆነ ነገሮችን እያመረተ ይገኛል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ግብዓቶችንም ሆነ ማቴሪያሎች የሚመረቱ እዚሁ ሀገር ውስጥ ነው። ኤክስፖ ከሚያደርጉ ድርጅቶች ጋር የተወሰኑ ምርቶች በሀገር ውስጥ የመተካት ሥራ እየሰራ ይገኛል። ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ አይነት ምርቶችን እየጨመረ ይገኛል። በተጨማሪም አሁን ላይ በአዲስ ምርት ለከብት እርባታ የሚውሉ እና ከብቶች የሚተኙበት ምንጣፎች ማምረት ጀምሯል። በሁሉም ዘርፎች ላይ የምንችለውን ለመስራት ጥረት እያደረግን ነው።

በተለይ ለሕፃናት እየገጣጠሙ የሚጫወቱበት እና በየመሥሪያ ቤቶች እየተቋቋሙ ላሉ የሕፃናት ማቆያዎች ውስጥ ምንጣፍ የሚውሉ ምርቶች በማምረት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል ይላሉ።

ድርጅቱ ለግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎችን የሚያመርት ሲሆን፤ ለሚመረተው ግብዓት የሚውሉ የተወሰኑ የምንዛሪ እጥረቶች እንዳሉ ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን ማምረት በሚቻለው አቅም እያመረተ መሆኑን ጠቅሰው፤አሁን ላይ ፋብሪካ መስራት ከሚችለው 20 እና 30 በመቶ ያህሉን ብቻ እየሠራ መሆኑን አቶ ሳምሶን ያስረዳሉ።

ድርጅቱ የሀገር ውስጥ ምርቶችን እንደማምረቱ አሁን ላይ ያለው የገበያ ትስስር የተሻለ ነው ያሉት አቶ ሳምሶን፤ ‹‹በተለይ ኤክስፖ ላይ መሳተፍ ከጀመርን ጀምሮ የተለያዩ ድርጅቶች የመገናኘት እድል የተፈጠረ መሆኑን ይበልጥ የገበያ ትስስርን መፍጠር ችለናል። ቀደም ሲል ከውጭ የሚያስገባቸው ግብዓቶች ከኛ እየገዙ ያሉ የጫማ ፋብሪካዎች እንዳሉ ሆኖ ኤክስፖ ላይም ጥሬ እቃዎቻችንን ፈልገው የሚገዙ ፋብሪካዎች አሉ›› ይላሉ።

ኤክስፖ የተሻለ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደረገና የተሻለ እድሎች የተገኘበት መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይም የማምረት ሥራው የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል ምርቶቻቸውን የገዙትም ሆነ አሁን ላይ ምርቶቻችን ለመግዛት የሚፈልጉ አካላት ስለምርቶች የሚሰጡት አስተያየት ምርቶቹ ጥራት ያላቸው እና ለረጅም ጊዜ እንደተገለገሉባቸው ይጠቅሳሉ። ኤክስፖርት የሚያደርጉት ሳይቀር የተወሰነ ግብዓቶች ከእነርሱ እየወሰዱ እየተኩ ኤክስፖርት እንደሚያደርጉ አመላክተዋል።

‹‹በጥራት ደረጃ ምንም የማይወጣለት ጥራት ያለው ምርቶች ነው የምናመርተው›› የሚሉት አቶ ሳምሶን፤እንዲያው ጥራት የሌላቸው ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ስላሉ ኅብረተሰቡ እነዚህ የሀገር ውስጥ ምርቶች እየመሰሉት አስተያየት ሲሰጥ ይስተዋላል። ነገር ግን ኤርጌንዶን ብራንድ አይቶ የገዛ ደግሞ ምርቱ ጥራት ያለው ለረጅም ጊዜ የተገለገለበት መሆኑን ይመሰክራል፤ ከዚህ በሻገር ኤርጌንዶ የሚለውን ስም ብዙዎች እንደ ቤተሰብ አድርጎ ያዩታል ብለዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ አሁን ላይ ምርቶቹን ወስደው የሚሸጡ አከፋፋዮች ያሉ ሲሆን፤ ወደፊት የራሱን መሸጫ ሱቆች ከፍቶ ምርቶች ለመሸጥ አቅዶ እየሰራ ነው። ድርጅቱ ባለው አቅም የማምረት አቅሙ ውስን ሆኖ እንኳን 150 እስከ 200 የሚደርሱ ሠራተኞች በስሩ ይገኛሉ። አቅሙን አጠናክሮ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ደግሞ ከ500 በላይ ለሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጥራል።

እስካሁን ይህ እንዳይሆን ያደረገው የምንዛሪ እጥረት እና የገበያ ክፍተት ሰው ከሀገር ውስጥ ምርት ይልቅ ለውጭ ምርቶች የነበረው ፍላጎት ከፍተኛ እንደነበር አስታውሰዋል። ‹‹አሁን ግን የሰው አመለካከት እየተቀየር የእኛን ምርት መርጠው ይመጣሉ። በጥራት ሆነ በዋጋ ደረጃ የኛ የተሻለ መሆኑና የውጭውን ገዝተው የሀገር ውስጥ ሲያነጻጽሩት ዋጋችንም እጅግ ተመጣጣኝ በመሆኑ ብዙዎቹ ይገረማሉ። አሁን ላይ ግን በጣም የተሻሉ ነገሮች አሉ›› ብለዋል።

ኤክስፖው የገበያ ትስስር ከማስገኘቱ ባሻገር ምርቶቹን የተጠቀሙት ሰዎች ድርጅቱን እንደ ቤተሰብ እንዲያዩ ያደረገ ነበር ያሉት አቶ ሳምሶን፤ ወደፊት የሚመረቱ ምርቶችን አይነት በመጨመር በሕፃናትና አረንጓዴ አሻራ ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች መኖራቸው ጠቅሰው፤ የበለጠ ሥራዎች እንዲያስፋፉ እድል እንደተፈጠረላቸው ጠቁመዋል። ከተወሰኑ ድርጅቶች ጋር ባደረጉት የገበያ ትስስር ብዙ የገበያ እድሎች ገበያ ያገኙበት መሆኑን አብራርተዋል።

በቀጣይ ወደ ኤክስፖርት ለመግባት ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ሳምሶን፤ ምርቶቹን በደንብ በማምረት የሀገር ውስጥ ገበያ በቂ ሁኔታ ተደራሽ በማድረግ ለኤክስፖርት ዝግጅት መደረጉን ይገልጻሉ ።‹‹አሁን ላይ ሁኔታዎች እየተስተካከሉ እየመጡ ስለሆነ ወደፊት የተሻለ እድሎች እያገኘን እንመጣለን። በተለይ መንግሥት የሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲገዙ እያበረታታ መሆኑ በጣም አጋዥ ስለሚሆን በቀጣይም በክልሎች ተደራሽነት እያሰፋን እንመጣለን›› ብለዋል።

**በተለይ ለሕፃናት እየገጣጠሙ የሚጫወቱበት እና በየመሥሪያ ቤቶች እየተቋቋሙ ላሉ የሕፃናት ማቆያዎች ውስጥ ምንጣፍ የሚውሉ ምርቶች በማምረት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል ይላሉ**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ጽዱ አዲስ አበባ፤ ጽዱ ኢትዮጵያ

**ዋሰልኝ አየለ**

በንጽህና እና በድምጽ ብክለት ጉዳይ ላይ ስንት ጊዜ እንደጮህን የዚህ ጋዜጣ ሰነዶች ምስክር ናቸው:: በግሌ አሜሪካ ወይም አውሮፓ ሀገራት መኖር የምመኘው ፒዛና በርገር ለመብላት ወይም ፈጣን የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለመጠቀም አይደለም:: ከዚህ በላይ የሚያጓጓኝ ንጹህ አየር መተንፈስ ነው:: የዓለም ምርጥ የአየር ንብረት ያላት ሀገር ውስጥ ሆኖ፣ ተፈጥሮ ያዳላላት የሚመስል ምቹ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር ውስጥ ተቀምጦ፤ በሰው ሰራሽ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሀገራትን አየር መናፈቅ ምንኛ መረገም ይሆን?

በቅርቡ የጽዱ ኢትዮጵያ ዘመቻ ተጀምሯል:: አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ የሰሞኑ የአየር ሁኔታ ንፋስና ፀሐይ የበዛበት ነው፤ በኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ ይህ የተለመደ የግንቦት ወር ባህሪ ነው:: ተፈጥሯዊ ክስተት ነው:: ሌላኛው አጋጣሚ በኮሪደሩ ልማት ምክንያት የግንባታ ሥራዎች ስላሉ መንገዶች አቧራ የበዛባቸው ናቸው:: ይህ ለጥቂት ጊዜ ስለሆነ በተስፋ እናልፈዋለን:: የግንቦት ወር ፀሐያማ መሆኑ ደግሞ የተፈጥሮ ፀጋ ነው::

አደገኛ የሆነው ግን ይህ ሳይሆን በሰው ሰራሽ መንገድ ያበላሸናቸው ነገሮች ናቸው:: ከተፈጥሯዊው የአየር ሁኔታ ጋር ተዳምሮ ብዙ ሰዎች በተደጋጋሚ ጉንፋን እና መሰል በሽታዎች ይይዛቸዋል:: ጉንፋን ቀላሉ ነው፤ ብዙ ሰው የአስም ህመምተኛ ነው:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በቆሻሻ በሚፈጠር መጥፎ ሽታ ነው::

አዲስ አበባ ውስጥ አፍንጫ ሳይያዝ የሚታለፉ ወንዞች የሉም:: ቱቦ ባለበት ቦታ ያለፈ ሁሉ ጉንፋን ተይዞ ወይም ከፍተኛ የራስ ምታት አጋጥሞት ነው የሚያልፈው:: ድልድዮች ባሉበት ሁሉ አጸያፊ ነገር እያዩ ማለፍ የተለመደ ነው:: በየቦታው ሽታ አለ:: በተለይ በእንዲህ አይነቱ የግንቦት ወር ከፍተኛ ነፋስና ፀሐይ ያለበት ስለሆነ ለብዙ በሽታዎች አጋላጭ ነው:: የዝናብ ወቅት ሲሆን ቢያንስ ዋና ዋናውን ዝናብ ሊያጥበው ይችላል፤ ሽታውም የከፋ አይሆንም::

ይሄ ሁሉ የሆነው እንግዲህ በግንዛቤ ማጣት ነው:: በሰው ሰራሽ መንገድ ነው እየታመምን ያለነው:: የጽዳት ባህላችን ደካማ ስለሆነ ነው:: የዕለት ከዕለት ሥራ መሆን የሚገባውን ጽዳት፣ በዘመቻ ነበር የምናጸዳው:: አሁን የተጀመረው የዘላቂ መፍትሔ ዘመቻ ይህን ችግር ሙሉ በሙሉ ባይቀርፍ እንኳን ይቀንሳል ማለት ነው:: አርዓያ ይሆናል ማለት ነው::

ብዙ ነገሮችን የምናደርገው ዓመት ጠብቀን ነው:: ለምሳሌ ዕቅድ የምናወጣው አዲስ ዓመት (መስከረም) ሲደርስ ነው:: መስከረም ካለፈ በኋላ፤ እንኳን አዲስ ዕቅድ ማውጣት የታቀደውም ይረሳል:: የበጎ አድራጎት ሥራዎችን (ለምሳሌ ህሙማንንና አቅመ ደካሞችን መርዳት) የምንሰራው እንደ እንቁጣጣሽ፣ ገና፣ ፋሲካ፣ መውሊድ ወይም አረፋ ያሉ በዓላት ሲመጡ ነው:: እነዚህ በዓላት ሲያልፉ ይረሳል::

ብዙ ነገሮችን የምናደርገው አሁንም ሁነት ጠብቀን ነው:: እስከ ዛሬ በነበረው ልማድ ከተሞች የሚጸዱት በከተማዋ ውስጥ የሆነ ዝግጅት የሚደረግ ከሆነ ነው:: ያ ዝግጅት ሲያልፍ ግን አይቀጥልም፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ በዝግጅቱ ምክንያት የወዳደቁ ተረፈ ምርቶች የሚያቆሽሹት ይበልጣል::

በየዓመቱ ‹‹ህዳር ሲታጠን›› እየተባለ በየቦታው ቆሻሻ ይቃጠላል (ሌላ ቀን አይደረግም እንጂ)፤ ዋና ዓላማውም ቆሻሻን ማቃጠልና ጽዱ አካባቢ መፍጠር ነው::

እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች የማንቂያ ምክንያት ይሆኑናል:: ቢያንስ በእንዲህ አይነት አጋጣሚ እንኳን አስታውሰን መነቃቃት ቢፈጠር ማለት ነው:: ልቦና ቢሰጠን ደግሞ በዚያው ቢለምድብን ጥሩ ነበር፤ ግን አልሆነም:: ስለዚህ አሁን የሚሰሩት ቋሚ የሆኑ ግንባታዎች የተሻለ መነቃቃት ይፈጥራሉ ማለት ነው:: ሌሎችንም ለመሥራት ያነሳሳል::

በተሻለ ሁኔታ አዲስ አበባ ንጹህ የምትሆነው ግን በማጽዳት ብቻ ሳይሆን ባለማቆሸሽ ነው:: የከተማዋ ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ ሁሉንም ቆሻሻ ጠራርጎና አጽድቶ ቢገባ የአስተሳሰብ ለውጥ ከሌለ በአንድ ቀን ማበላሸት ይቻላል:: በየቦታው መጸዳጃ ቤቶች ቢዘጋጁም የአዕምሮ ንቃቱ ከሌላ መጸዳጃ ቤት ላለመግባት ብሎ ብቻ መንገድ ላይ የሚሸና ሊኖር ይችላል:: የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫዎች ቢዘጋጁም ህሊናው የማይሰራ ሰው ሜዳ ላይ ሊጥለው ይችላል::

የወንዝ ዳርቻዎች ጥሩ ምሳሌ ይሆኑናል:: በክረምት ጎርፍ ጠራርጎ ሲወስደው ወንዙ ንጹህ ይሆናል፤ ወዲያውኑ ግን ረፋድ እንኳን ሳይሆን አፍንጫ ተይዞ የሚታለፍበት ይሆናል:: በግንብ እና በአጥር ዙሪያ ያለው አፍንጫ የሚበረቅስ መጥፎ ሽታ አብሮ የተገነባ አልነበረም፤ በሰዎች ሽንት እና የቆሻሻ መጣያነት ነው እንደዚያ የሚሆነው:: ይህ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ስናየው የቆየነው ነው:: አሁንም እየተገነቡ ባልሆኑ ወንዞች አካባቢ አለ::

የሚያቆሽሸውን ያህል በዚያው መጠን ደግሞ ቶሎ ቶሎ የሚያጸዳ ቢኖር ችግሩ ይቀንሳል:: ልብ ብላችሁ ከሆነ ብዙ ጊዜ ሽንት የሚሸናው ከዚህ በፊት የተሸናበት ቦታ ላይ ነው፤ ቆሻሻ የሚጣለው ቆሸሾ የሚታይ ቦታ ላይ ነው:: የያዝነውን ሶፍት እንኳን ንጹህ ቦታ ላይ ለመጣል ይከብደናል:: ቆሻሻ ቦታ ከጠፋ ብዙ ሰው ሊጥለው ያሰበውን ነገር በኪሱ ይከተዋል፤ ቆሻሻ ያለበት ቦታ ለመጣል ማለት ነው:: እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ሁሉም አካባቢ ንጹህ ቢሆን ሁሉም ለንጽህና እንደሚበረታታ ነው::

የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ? ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቀረ ቢሆንም የፕላስቲክ ውሃ የታሸገበትን ወረቀት ለመጣል ዘወር ዘወር ብለው ያያሉ:: የተጣለ ካለ ሁሉም ይጥላል:: የተጣለ ከሌለ ግን ፕላስቲኩ ወገብ ላይ ካለው ሽፋን ውስጥ ያደርጉታል፤ ወይም ኪሳቸው ይከቱታል (እኔ ብዙ ቀን ኪሴ ከትቻለሁ):: መሬት ላይ በመጣል የሚጀምረው አንድ ሰው ነው ማለት ነው፤ ከዚያ በኋላ መቼም አንዴ ተጥሎበታል በሚል ሁሉም እየጣለ ወለሉ የፕላስቲክ ፋብሪካ ይመስላል:: ለምሳሌ አነሳሁት እንጂ የውሃ ፋብሪካዎች የክዳኑን መሸፈኛ አስቀርተውታል::

እነሆ ይህ በዘመቻ ብቻ የሚደረግ የጽዳት ባህላችን ለውጥ ሳያመጣ ቀርቶ በእንዲህ አይነቱ ነፋስና ፀሐይ በሚበዛበት የግንቦት ወር ጉንፋን በጉንፋን ስንሆን ቆይተናል:: በመንደሮች መካከል ባሉ የውስጥ ለውስጥ በዮች ሁሉ መጥፎ ሽታ አለ::

የሚያሳዝነው ግን የተማረ የሚባል ሰው ባለበት ሁሉ አስነዋሪ ነገር የሚታይ መሆኑ ነው:: ይሄ በትልልቅ የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ሳይቀር የታዘብኩት ነው:: በእንደዚያ አይነት ተቋም ውስጥ ቢያንስ መጻፍና ማንበብ የማይችል የለም፤ በብዛት ደግሞ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ነው:: ምንም እንኳን ጥፋቱን የሚፈጽመው ጥቂት ሰው ሊሆን ቢችልም መጸዳጃ ቤት ውስጥ የሚታየው ነገር ከላይ እስከ ታች ምን ያህል ኋላቀር እንደሆንን ያሳያል::

በቅርቡ በመንግሥት የተጀመረው የጽዱ ኢትዮጵያ ዘመቻ ከምንም በላይ የሚጠቅመው አርዓያነቱ ነው:: የሚሰሩት መጸዳጃ ቤቶች ሁሉንም ያዳርሳሉ ማለት አይደለም፤ ግን ሌሎች እንዲሰሩ ያነሳሳሉ:: መጸዳጃ ቤቶች ተሰሩ ማለት ችግሩ የመጸዳጃ ቤት ብቻ ነበር ማለት አይደለም:: አጠቃላይ የንፁህነትን መንፈስ ይፈጥራል:: የህሊና መነቃቃትንም ይፈጥራል:: በአግባቡ ካልያዝነው የተፈለገውን ውጤት አያመጣምና የጽዱ ኢትዮጵያ ግንባታዎች ሲሰሩ አስተሳሰባችንም ጽዱ ይሁን!

# ዓለም አቀፍ

## የቢቢሲ የምርመራ ዘገባን ተከትሎ ታዳኙ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪ በቁጥጥር ስር ዋለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቢቢሲ ምርመራ ዘገባን ተከትሎ በአውሮፓ በጣም ተፈላጊ የሆነው ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪው ኢራቅ ውስጥ በቁጥጥር ስር ዋለ።

ባርዛን ማጂድ ያለፈው እሑድ ጠዋት በኢራቋ ኩርዲስታን ውስጥ በቁጥጥር ስር መዋሉን አንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን ተናግረዋል።

ግለሰቡ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ለበርካታ ዓመታት በእንግሊዝ ቻናል በኩል በጀልባ እና በጭነት መኪኖች ስደተኞችን በህገወጥ በማዘዋወር ይታወቅ ነበር።

ቢቢሲ ‘ስኮርፒዮን’ (ጊንጡ) በመባልም የሚታወቀውን ማጂድን በሺህዎች የሚቆጠሩ ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ እንዳጓጓዘ በሚታመንባት ሱለይማንያ ከተማ ድረስ ተከታትሎ አግኝቶታል።

“ምናልባት አንድ ሺህ ምናልባትም 10 ሺህ ሊሆኑ ይችላል። ስላልቆጠርኩ በትክክል አላውቀውም” ብሏል ስላዘዋወራቸው ሰዎች ቁጥር ሲናገር።

ማጂድን በቁጥጥር ስር ለመዋል የቢቢሲ ምርመራን መጠቀማቸውን የኩርዲስታን ክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት ተናግረዋል።

ባለሥልጣኑ “ዛሬ ጠዋት 1 ሰዓት ላይ በቁጥጥር ስር የዋለው ከቤቱ ደጃፍ ነው። ከቤቱ በወጣበት ቅጽበት ያለምንም ችግር ነው የያዙት” ሲሉ ያለፈው እሁድ የተያዘበትን መንገድ አብራርተዋል።

“በመጀመሪያ በእሱ ላይ የሚቀርቡትን ክሶች እዚህ እየተመለከትን ነው። ቀጥለን ከአውሮፓ ፖሊሶች እና አቃብያነ ህግ ጋር እሱን ለመክሰስ በሚቀርበው ጉዳይ ላይ እንወያያለን።”

የዩናይትድ ኪንግደም ብሔራዊ የወንጀል ኤጀንሲ (ኤንሲኤ) ግለሰቡ በቁጥጥር ስር መዋሉን አረጋግጧል።



ባርዛን ማጂድ



“ቢቢሲ ጉዳዩን ይፋ በማውጣቱ እናመሰግናለን። ሰዎችን ወደ እንግሊዝ በማዘዋወር ላይ የተሰማሩ የወንጀል መረቦችን ለመበጣጠስ እና ለመስበር የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠናል” ሲል መግለጫው አክሏል።

እአአ ከ2016 እስ 2021 መካከል ባለው ጊዜ የስኮርፒዮን ቡድን በአውሮፓ እና በእንግሊዝ መካከል ያለውን አብዛኛውን የሰዎች ህገ ወጥ ዝውውር እንደተቆጣጠረ ይታመናል።

ሁለት ዓመት በፊጀ ዓለም አቀፍ የፖሊስ ዘመቻ በዩናይትድ ኪንግደም፣ በፈረንሳይ እና በቤልጂየም ፍርድ ቤቶች 26 የቡድኑ አባላት ላይ የቅጣት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል።

ስኮርፒዮን ግን ለመደበቅ ችሎ ነበር።

እሱ በሌለበት በቤልጂየም ፍርድ ቤት 121 ሰዎችን በማዘዋወር ወንጀል ተከሷል። በኋላም የ10 ዓመት እስራት እና 968 ሺህ ዩሮ ቅጣት ተበይኖበት ነበር።

ቢቢሲ እስኪያገኘው ድረስ ስኮርፒዮን የት እንዳለ አይታወቀም ነበር።

በሚያዝያ ወር በስልክ በነበረ ቆይታ ማጂድ በባሕር ሲጓዙ ለሰመጡ ስደተኞች ብዙም ርህራሄ ያለው አይመስልም ነበር።

“መጨረሻህን አምላክ ያውቃል። ይህ ግን አንዳንድ ጊዜ የአንተም ጥፋት ሊሆን ይችላል። አምላክ በጀልባ ሆናችሁ አቋርጡ አይልም” ብሏል።

በመጨረሻም ከቢቢሲ ጋር ሱለይማንያ በሚገኝ የገበያ አዳራሽ ለመገናኘት ፈቃደኛ ሆነ።

ከቢቢሲ ጋር በነበረው ቆይታ በዚህ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር የወንጀል መረብ ውስጥ ትልቅ ሚና የለኝም ሲልም ቃሉን ሰጥቷል። ሌሎች የቡድኑ አባላት እሱን ተጠያቂ ለማድረግ ሞክረው እንደነበርም ተናግሯል።

“የተወሰኑ ሰዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ ‘እኛ ለእሱ እየሠራን ነበር የሚል ምላሽ ሰጥተዋል ፤ይህንንም ያሉት ቅጣቱ እንዲቀንስላቸው ፈልገው ነው ብሏል።

በመቀጠልም ማጂድ ከስደተኞች ጋር የሚሠራውን እና ከቢቢሲ ጋር በምርመራው ላይ የተሳተፈውን የቀድሞ የጦር አባል ሮብ ላውሪንን በሱለይማንያ ያደረገውን የገንዘብ ልውውጥ እንዲያይ ጋበዘው።

“ማንም አላስገደዳቸው። ፈልገው ነው። እባካችሁ ይህን አድርጉልን እያሉ አዘዋዋሪዎችን እየለመኑ ነበር። ... አዘዋዋሪዎች ለአምላክ ሲሉ ሌላ ሀገር ይሰዷቸዋል። ከዚያ የማይሆኑ ነገሮች ማለት ይጀምራሉ” ብሏል።

በቤልጂየም የሚገኘው የአቃቤ ህግ ቢሮ አባል የሆኑት አን ሉኮቪያክ ግለሰቡ በቁጥጥር ስር የመዋሉን ዜና በደስታ ተቀብለዋል።

“እሱ በአካል ተገኝቶ መልስ እየሰጠ በመጨረሻ በዚህ ጉዳይ ላይ ፍትህ ሲገኝ የማየት ዕድል አለን።” ብለዋል።

ዜና

# "ባለሥልጣኑ የዓለም ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ምርምር ጉባዔ ትናንት ተጀምሯል።

ሚኒስትሯ ጉባዔውን በንግግር ሲከፍቱ እንዳሉት፤ የቅርስ ምርምር ፈረጀ ብዙና ሁሉንም የዕውቀት መስኮች የሚዳስስ በመሆኑ ባለሥልጣኑ በቅርስ ምርምር የልህቀት ማዕከል በመሆን በሀገራችን ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ አርዓያ ለመሆን ታላቅ ራዕይ ይዞ መንቀሳቀስ ይገባዋል።

ምድረ ቀደምት የሆነችው ኢትዮጵያ የበርካታ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት ናት ያሉት ሚኒስትሯ፤ እነዚህ የማንነታችን መገለጫ፣ የሀገራችን መለያና ኩራት የሆኑ ቅርሶች በዘመናት ሂደት ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግረው ከዘመናችን ደርሰዋል ብለዋል።

አደራ የተቀበልነው እኛም ቅርሶችን ዘመናችን የደረሰበትን የእድገት ደረጃ በሚመጥን መንገድና ሥነ-ዘዴ መዝግበን፣ ተንከባክበን፣ ጠብቀንና አልምተን ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የሀገራችንን ቅርስ የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ የማልማት ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን አስታውሰው፤ ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ከበፊቱ ይልቅ ብዙ ሥራዎች እንደመሚጠብቁት ጠቁመዋል።

በተለይም የዲጂታል ቴክሎጂን ከመጠቀም፣ ሀገራችንን የሚመጥን ሙዝየም ከመገንባት፣ ከማደራጀትና ፈርጀ ብዙ የሆነ የቅርስ ምርምር ከማድረግ አኳያ ብዙ ሥራዎች በፍጥነት ሊሠሩ ይገባ ብለዋል። ለዚህም ቱሪዝም ሚኒስቴርም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር ናሲሴ ገለጻ፤ ለውጡን ተከትሎ መንግሥት ለቅርስ እንክብካቤና ልማት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ላይ ይገኛል። ቅርስ ትልቅ የሀገር ሀብት እንደመሆኑ መጠን በተገቢው ሁኔታ ተጠብቆና ለምቶ በየደረጃው ለሕዝብ ጥቅም ማስገኘት ይኖርበታል።

ይሁን እንጂ ሀገራችን ካላት የቅርስ ብዛትና ዓይነት አንፃር መልማት የቻሉት እጅግ ጥቂት በመሆናቸው የተነሳ ከቅርስ የሚገኘው ገቢ እጅግ አነስተኛ ነው ብለዋል።

መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ሲያደራጅ ቱሪዝምን በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ ለብቻው ያቋቋመውና ከአምስቱ የኢኮኖሚ ሴክተሮች አንዱ ያደረገው ዘርፉን ለማሳደግ መሆኑን አንስተዋል።

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን አቅም ካሳነሱት እክሎች ዋነኛው የተጠናከረ የቅርስ ምርምር ክፍል አለመኖሩ ነበር ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከምዝገባ ጀምሮ እስከ ልማት ያለው በቅርስ ላይ የሚደረግ ሥራ ያለምርምር የትም ሊደርስ አይችልም ሲሉ ገልጸዋል።

ችግሩን በመረዳት መንግሥት የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣንን በልዩ ሁኔታ በመመልከት የቅርስ ምርምር በመሪ ሥራ አስፈጻሚ ደረጃ እንዲደራጅ መደቦችም ከጀማሪ እስከ መሪ ተመራማሪ እንዲፈቀድለት አድርጓል ብለዋል።

ስለሆነም በዘርፉ የልህቀት ማዕከል መሆንና በምርምር ታላቅ ተሞክሮ ካላቸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር ሊሠራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ዓመታዊ የቅርስ ምርምር ጉባዔ ዛሬ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ የጉባዔው አካል የሆነ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ጉዞና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች የሚያሳይ አውደ ርዕይም ተከፍቷል።

# የመካከለኛው ምስራቅ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሙስና፣ የኑሮ ውድነት፣ ስደት እንዲሁም በሽብርተኝነት ለምትናጠው የአፍሪካ ቀጣና አዲስ የመከራ ቀንበር ይዞ የሚመጣ ነው የሚለው የብዙዎች ግምት ነው። የጦርነቱ መዘዝ ለአፍሪካ አህጉር የሚተርፍ በመሆኑ አህጉሪቱ የሚበጃትን የቤት ሥራዎች በማከናወን ጉዳዩን በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት የዘርፉ ሙሁራን ይናገራሉ።

ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ተመራማሪና የአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ ጉዳዮች ተኝታኝ በፍቃዱ ቦጋለ (ፕ/ር)፤ በመካከለኛው ምስራቅ የሚነደው እሳት በአፍሪካ ቀጣና ከፍተኛ የደህንነት ስጋት የደቀነ ነው ይላሉ። ይህም ውጥረት ጉዳት እንዳያስከትልም ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

እንደሀገርም ሆነ እንደ ቀጣና ችግሩ በንግግር መፈታት አለበት የሚለውን መርህ በመደገፍ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነም ይናገራሉ።

ከብዙ ቀጣናዊ ጉዳዮች አንጻር ገለልተኛ መሆን አዋጪ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር በፍቃዱ፤ ከሁለቱ አንዱን ደግፎ በግልጽ አቋም መያዝ ከጉዳት ውጪ ይዞት የሚመጣው ጠቀሜታ እንደሌለ ያስረዳሉ።

በመካከለኛው ምስራቅ ባለው ውጥረት አንዳንድ ሀገራት የያዙት የወገንተኝነት አቋም ወደ ኢጋድና አፍሪካ ህብረት እንዳይመጣ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል ባይ ናቸው።

ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ትኩረትን የሚስብ በመሆኑ ቀጣናው አንድ አቋም የሚይዝ ከሆነ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲዊ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱ የማያጠራጥር ነው። ይህም ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጫና የሚያስከትል እንደሚሆን መገንዘብ የግድ እንደሚል ይገልጻሉ።

ጦርነቱ በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ሌላ ስጋት እያዋለደ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ በተለይ ቀይ ባህር በርካታ ሀገራት የወጪና የገቢ ምርት የሚጠቀሙበት በመሆኑ በመመካከለኛው ምስራቅ ውጥረት ከመከሰቱ ጀምሮ የባህር ላይ ውንብድና እንደተበራከተም ያክላሉ።

አሁን ላይ ህንድ እስከ ቀይ ባህር ጫፍ ድረስ የጸጥታ አካላትን በማሰማራት የባህር ላይ ወንበዴዎችን እየተዋጋች ትገኛለች፤ በዚህም የአፍሪካ ሀገራት ድጋፍ መስጠትና በማጠናከር ረገድ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ንግዶችና በቀይ ባህር ደህንነት እንዲሁም ሽብርተኝነትን በመዋጋት ዙሪያ ከምን ጊዜውም በላይ ትብብር ማድረግ ከወዲሁ የሚጠበቅ ነው።

በመካከለኛው ምስራቅ የተከሰተው አለመረጋጋት አፍሪካን የሚጎዳ በመሆኑ የአፍሪካ ሀገራትም ሆነ በሥራቸው ያሉ ተቋማት ስለጉዳዩ አሳሳቢነት በመረዳትና በመምከር አንድ አቋም መያዝ ይኖርባቸዋል የሚሉት ደግሞ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ናቸው።

በኢትዮጵያም ደረጃ ሰላምና መረጋጋትን ዘላቂ ለማድረግ እያንዣበበ ያለውን ጦርነት ከግምት ውስጥ ማስገባትና ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የቀጣናው ሀገራትም አስቸኳይ ስብሰባ አድርገው በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እንዲሁም በሚሊተሪ የሚያስከትለውን መዘዝ ገምግመው ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል ይላሉ።

የመጀመሪያው ሰላም እንዲሰፍንና ጦርነት እንዳይስፋፋ የሚያደርጉትን ጥረት አጠናክሮ ማስቀጠል እንዲሁም ይዞት የሚመጣው መዘዝ ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት ምን ዓይነት አማራጭ መጠቀም ያስፈልጋል በሚለው ጉዳይ ላይ አንድ አቋም መያዝ ተገቢ ነው ባይ ናቸው።

"በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ውጥረት በመባባሱ ምክንያት ቀይ ባህር ሰላም አጥቷል፤ ይህም ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ከመጫሩም በላይ በየጊዜው በኑሮ ውድነት ለምትናጠው አፍሪካ ሌላ የዋጋ ንረት እየደቀነ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም በመካከለኛው ምስራቅ ቀጣና በየጊዜው የሚከሰቱ ጉዳዮች በቅርበት መከታተል ያስፈልጋል፤ ሲሉም ይገልጻሉ።

# ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ጌትነት ዘገየ ውቤ የሰሌዳ ቁጥር OR-01-04620 የሊብሬ ቁጥር 462448 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በቀን 24/08/2016 አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የመኪና ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ለአመልካች ሰሌዳ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የምእራብ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

# ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አብድረዛቅ ፈቱ የሰሌዳ ቁጥር 1- 35335 ደ/ሀ የሻንሲ ቁጥር MD2A25BXMWG70680 የሞተር ቁጥር AZXWMH59594 ተሽከርካሪ ባጃጅ ሞዴል RE-4S ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቀን 24/8/2016 አመልክተዋል፡፡ ታርጋ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ /ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ አመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የጉራጌ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

# አፋር ክልል

ንብረትነቱ አብዱ ሁሴን ያዮ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-00468 አፋ የሆነ ተሽከርካሪ የሞተር ቁጥር 5L-5253780 የሻንሲ ቁጥር LH172-1030675 የፊት ሰሌዳ ወድቆ የጠፋባቸው ስለሆነ ከፖሊስ ባቀረቡልን ማስረጃ መሰረት በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያሳወቅን በተባለው ጊዜ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የሚሰጣቸው መሆኑን እገልጻለን፡፡

**የአፋር መንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ**

# አዲስ አበባ አስተዳደር

ከሣሽ አቶ ተስፋዬ ዘሪሁን ለገሰ ተከሳሽ ወ/ሮ እማዋይ አራጌ ሙጬ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ 16/9/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 2 ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ምስጋኑ ጉተማ ቦንጋሴ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A03296 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSFXKN504046 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD61547*190807011687* የሊብሬ ቁጥር 0225305 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ2/9/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራኒዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፍቅር ትራንስፖርት ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-46337 የተሽከርካሪው አይነት አውቶቡስ (ከ11 የበለጠ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር LKLS1CSB47A125096 ሞዴል HIGERBUS-KLQ6728-MIDIBUS የሞተር ቁጥር 69462312 የሊብሬ ቁጥር 427663 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ17/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዲ ኤ ኤፍ ማተሚያ ቤት ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B52807 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር 6FPPXXMJ2PMB13684 ሞዴል RAPTOR (FORD) የሞተር ቁጥር YN2X2MB13684 የሊብሬ ቁጥር 474269/504236 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ የፊት እና የኋላ ጠፋብኝ ብለው በ29/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ ዘቢባ ዑመር እና በተከሳሽ አቶ አብዱልዋህድ አህመድ መካከል ስላለው የፍቺ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ አቶ አብድልዋህድ አህመድ በ 12/9/2016 ዓ.ም በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 5 እንዲቀርቡ ሆኖ ለ 13/9/2016 ዓ.ም በ 4፡50 በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ምድብ አስማሚ ቢሮ ቁጥር 303 እንዲቀርቡ የግራ ቀኙን ክስ ለመስማት ለ 16/9/2016 ዓ.ም 4፡40 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 4 ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ይከአሎ ጉዕሽ ገ/ማርያም የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C13900 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-3102858 ሞዴል GF-SCP10-AHPNK-D የሞተር ቁጥር 1SZ-0176039 የሊብሬ ቁጥር 438598/486023 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ3/9/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራኒዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ወንድአጥር መሸሻ በላቸው የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-28991 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRS30C160209 ሞዴል 380T38H የሞተር ቁጥር F3BE-06816-B274-058542 የሊብሬ ቁጥር 0305377 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ29/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከሳሽ አቶ ደረጀ አለማየሁ ተከሳሽ አቶ ፈዬ ንጉሱ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ/ሾች ለክሱ ያላቸውን መልስ ከነማስረጃው በፅሁፍ እና በሲዲ/ሶፍት ኮፒ/ በሬጅስትራር ፅ/ቤት ቢሮ ቁጥር B1 በኩል 12/09/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት እንዲያያይዙ እንዲሁም ለቃል ክርክር 14/09/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለሚ ኩራ ምድብ 8ኛ ፍታብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ወንድአጥር መሸሻ በላቸው የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-02929 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር ZAHE3KAARR0950013 ሞዴል ZAHE3KAAR የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0157388/0234222 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ29/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራኒዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የግዕዝ የኮምፒዩተር ፅሁፍ አባትና የእንስሳት ሐኪም

**ክብረአብ በላቸው**

በተሠማሩበት የሙያ መስክና ምርምር ግሩም ሥራ በመሥራት የሀገራቸውን ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስጠሩና ታሪካቸውን በደማቅ ቀለም ማፃፍ የቻሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ጥቂት አይደለም። ከእነዚህ እንቁ ግለሰቦች መካከል የግዕዝ የኮምፒዩተር ፅሁፍ አባትና የእንስሳት ሐኪሙ ዶክተር አበራ ሞላ አንዱ ናቸው።

የተወለዱት በቀድሞው የሸዋ ጠቅላይ ግዛት መናገሻ አውራጃ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሰንዳፋ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሰንዳፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በደብረ ብርሃን ከተማ ኃይለማርያም ማሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።

የከፍተኛ ትምህርታቸውን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው የውጭ የትምህርት ዕድል በማግኘታቸው ኬንያ ናይሮቢ ሄደው ተምረዋል። በመቀጠልም ወደ ሰሜን አሜሪካ በማቅናት ተጨማሪ ትምህርት ተምረው አጠናቀዋል።

ዶክተር አበራ ወደ ሥራው ዓለም በመቀላቀልም በሀገር ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ የዓለም ሀገራት በተለይም በአሜሪካ በርካታ ሥራዎችን የሠሩ ታላቅ ምሁር ናቸው። በሥራቸውም ከዓለም የእንስሳት ሐኪሞች አንዱ ለመሆን በቅተዋል። የግዕዝ ፊደልን በኮምፕዩተርና በተንቀሳቃሽ የእጅ ስልክ በማስገባት መጠቀም እንዲቻል በማድረጋቸውም ሰባት የዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካና የኢትዮጵያ የባለቤትነት መብት ለማግኘት የቻሉ ሊቅ ናቸው። ከእዚህ ባለፈ የግዕዝ አልቦ አሃዝ ቀለሞችና የግዕዝ አሥር ቤት አኃዛዊ ቍጥሮች ፈጠራንም የሠሩ ሰው ናቸው። ለእነዚህ ለሠሯቸው ታላቅ ሥራዎችም በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ለመቀበል ችለዋል።

አማርኛ ቋንቋን ጨምሮ የግእዝ ፊደላትን ለጽሑፍ አገልግሎት የሚጠቀሙ ቋንቋዎች የጽሑፍ አሊያም የትየባ ስልት በሥነ ቴክኒኩ ዘርፍ ወጥነት አይስተዋልበትም። በግእዝ ፊደላት በኮምፒውተር ለመጻፍ የሚያገለግሉ ሶፍትዌሮችን የሚያበለጽጉ ተመራማሪዎች የሚመሩበት የጋራ መስፈርት ባለመኖሩም አንደኛው ጽሑፍ ከሌላኛው ጋር ሲጣረስ ይታያል። እንዲያም ሆኖ በኮምፒውተር እና ሌሎች ዘመናዊ የሥነ-ቴክኒክ ውጤቶች ላይ ፊደላቱን ጊዜ እና ጉልበትን በመቆጠብ አቀላጥፎ ለመጻፍ የማስቻል የሶፍትዌር ማበልጸግ ሙከራዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች ሲደረጉ ይስተዋላል።

ዶክተር አበራ በኮምፕዩተር ግዕዝ ፊደልን መጠቀም እንዲቻል ያደረጉት የአማርኛውን የጽሕፈት መሣሪያ (ታይፕራይተር) ለሚያውቁት ቀላል እንዲሆን በ"a"፣ "b"፣ "c"፣ "d" ምትክ "ሀ"፣ "ጠ"፣ "ሸ"፣ "ዘ" እና እንግሊዝኛ ለሚያውቁ በ"A"፣ "B"፣ "C"፣ "D" ምትክ "አ"፣ "በ"፣ "ቸ"፣ "ደ" ቀለሞችን በመመደብ ዓይነት ሠላሳ ሰባቱን የግዕዝ ቤት ጎኤያት ለ37 የኮምፕዩተር መርገጫዎች ስሞችም በማድረግ ነበር። ስምንቱን የፊደል ቤቶች ወይም እንዚራን ስምንት ፎንቶች ላይ በተኗቸው። በእዚህ ዘዴ በእጅ ጽሑፍና ማተሚያ ቤቶች ብቻ ይታተሙ የነበሩት የግዕዝ (Ethiopic) ፊደላት ለመጀመሪያ ጊዜ በኮምፕዩተር ተከተቡ።

መጀመሪያ መሥራት የሚቻለውም የአማርኛ ታይፕራይተር ዓይነቱን ቅጥልጥል ፊደል እንደ አማርኛው ታይፕራይተር በአንድ የላቲን ፊደል ምትክ መተካት ስለነበረ ያንን ስለልፈለጉ እንጂ ቅጥልጥሉንም ከማንም በፊትም ሊሠሩበት ይችሉ ነበር። ተሠርቶበታልም። እያንዳንዱ ቀለም አንድ-ወጥ የሆነውን የማተሚያ ቤቶች ዓይነት ትክክለኛ የግዕዝ ፊደላችንን ለመጀመሪያ ጊዜ በማቅረብና እያንዳንዱም በሁለት መርገጫዎች እንዲከተብ በመፍጠር ግዕዝ ከማተሚያ ቤቶች ወደ ኮምፒዩተር እንዲገባ አደረጉ። ሞድኢት (ModEth) በመባል የታወቀውን የቃላት ማተሚያ የማይክሮሶፍትን ዶስ በመጠቀም በአሜሪካ ውስጥ ለገበያ አቀረቡ።


ዶክተር አበራ ሞላ

ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሊቆች፣ ሚኒስትሮችና ደራስያን የእንግሊዝኛውን የታይፕ መጻፊያ ለአማርኛ መከተቢያ እንዲያገለግል ወደ ሰማንያ ዓመታት ግድም ሲመራመሩ ቆይተው ባይሳካላቸውም ዶክተር አበራ ጥረቶቻቸውን በኮምፕዩተር አሳክተዋል።

ዶክተር አበራ የግዕዝን ቀለም (Glyph) በኮምፒዩተር በቀላሉና በቀልጣፋ ዘዴ ማቅረብ ስለቻሉ ሕዝቡ ከማተሚያ ቤቶች በተሻለ ሁኔታ በፊደሉ መሥራት ችሏል። በእዚህም የተነሳ ሕዝቡ መጻሕፍትንና የመሳሰሉትን ለማሳተም በየማተሚያ ቤቶች ወረፋ ከመጠበቅና ከመንግሥት እገዳ ተርፎ የእራሱ አታሚ ሆኗል። ዘዴውም በአማርኛ ሳይወሰን ለሁሉም የግዕዝ ቀለሞች መከተቢያና ማተሚያ ከሌሎች የዓለም ፊደላት እኩልና ጎን በሚገባ ሥራ ላይ እየዋለ ነው።

የግዕዝ ኮምፒዩተራይዜሽን ፈር ቀዳጅ የሆኑት ዶክተር አበራ የኮምፒዩተርን ሃይል እና እምቅ አቅም የተገነዘቡ እና ከዘመኑ በፊት የነበሩ ባለራዕይ ናቸው፡፡ ከ1982 እኤአ ጀምሮ ወይም ላለፉት ዓመታት በግዕዝ ፊደል ኮምፒዩተራይዜሽንና የአፃፃፍ ዘዴ ላይ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡

ዶክተር አበራ እኤአ በ1982 ለመጀመርያ ጊዜ ግዕዝን በኮምፕዩተራይዝድ በማድረግ የግእዝ ስክሪን እና የፕሪንተር ፊደሎችን ለመሥራት አንድ ዓመት ፈጅቶባቸዋል። ይህም የተሳካው ከ400 በላይ የግዕዝ የፊደል ቀለማትን በስምንት የኮምፒዩተር ቁልፎች ላይ በዘዴ በማሰራጨት ነው። ጠቅላላ ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅም የፈጠሩት የመጀመሪያው የግዕዝ ኮምፒዩተራይዝድ የፊደል ገበታና የኮምፒዩተር መተየቢያ ሶፍትዌር በ1987 እ.ኤ.አ ይፋ ሆነ።

ዶክተር አበራ በፈር ቀዳጅነት የጀመሩት ጥረትና ፈጠራ ባይኖር ኖሮ የአማርኛና ግዕዝ ፊደላትን የኮምፒዩተር ፅሁፍ ማዘመን፣ በዩኒኮድ ደረጃ እንዲመደብ ማድረግና አሁን ያለውን በኮምፒዩተሮችና ኢንተርኔት ላይ አማርኛንም ሆነ በግዕዝ ፊደላት የሚፃፉ ቋንቋዎችን በቀላሉ ለመተየብም ሆነ ለማንበብ የሚያስችል መንገድ ላይ መድረስ ባልተቻለ ነበር።

በላቲን ፊደላት መተየቢያ የኮምፒውተር የጽሑፍ ገበታ ላይ ከ«ኤ» እስከ «ዜድ» 26 (A -Z)የተደረደሩ ፊደላት አሉ። ዶክተር አበራ ሞላ የኮምፒውተር የመጻፊያ ገበታ ላይ የሚገኙትን እነዚህን 26 የላቲን ፊደላት ጨምሮ ከ 1 እስከ 0 የተደረደሩ ቁጥሮችን እንዲሁም ቀሪ ምልክቶችን፤ በጥቅሉ 47 ምልክቶችን ልክ እንደ እንግሊዝኛው በግእዙም በአንድ ጥቁምታ እንዲጻፉ ማድረግ ችለዋል።

ዶክተር አበራ በአማርኛ ቋንቋ በሳድስ የሚነገሩ ቃላት በርካታ መሆናቸው ሳድስ ፊደላትን ኮምፒተር ገበታ ላይ በአንድ ምት ወይንም ጥቁምታ መተየብ የአጻጻፍ ፍጥነትን ያሻሽላል የሚል እሳቤ አላቸው። ለአብነት ያህልም ምግብ፣ ልብስ፣ ብርድ፣ ትምህርት፣ ድርቅ፣ የመሳሰሉት ቃላት ሙሉ ለሙሉ በሳድስ ድምጾች (ፊደላት) የሚጻፉ ናቸው። በተለምዶ ሳድስ ፊደላት በውስጣቸው የያዝዋቸውን አናባቢዎች በዶክተር ለማ የፊደል ገበታ መፃፊያ ስልት መተየብ አያስፈልግም።

ለአብነት ያህል ምግብ የሚለውን የአማርኛ ቃል ብንመለከት ኮምፒውተር ላይ ለመተየብ «ኤም»፣ «ኢ»፤ «ጂ»፣ «ኢ»፣ «ቢ»፣ እና «ኢ» የተሰኙትን በጥቅሉ ስድስት የላቲን ፊደላት መጠቀም ያስፈልጋል። ሆኖም ስድስቱን የፊደል ቍልፎችን ከመጫን ይልቅ አናባቢው «ኢ»ን በማስቀረት «ኤም»፣ «ጂ» እና «ቢ» ፊደላትን ብቻ በመጫን ምግብ የሚለውን ቃል በሦስት ፊደላት በአማርኛ መጻፍ እንዲቻል ነው ያደረጉት። ከ47ቱ የተቀሩት ፊደላት በሁለት ምት አለያም ጥቁምታ የሚጻፉ ናቸው።

ዶክተር አበራ ሞላ አዲስ ፈጠራ ተብሎ የባለቤትነት መብት ዕውቅና በዩናይትድ ስቴትስ ካሰጣቸው ሌላኛው እመርታ መካከል የኮምፒውተር የጽሑፍ ገበታ ላይ በላቲን ፊደላቱ «ኤ» እና «ኢ» 14 ቀለማትን እንዲጻፍ ማስቻላቸው ነው። ቀደም ሲል የመተየቢያ ገበታው ላይ ሁለቱ ፊደላት በሁለት ጥቁምታ አለያም ምት ሲጻፉ ፊደላቱ ሊሰጡ የሚችሉት ስድስት ቀለማትን ብቻ ነበር።

"ዶክተር አበራ እርስዎ የተማሩት የእንስሳት ህክምና ነው፤ እንዴት ወደ ኮምፒዩተር ትምህርት ሊያዘነብሉ ቻሉ ምክንያትዎ ምን ይሆን? " ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፡- " እንደሚታወቀው ኢትዮጵያውያን በርካታ ሀብቶች ያሉን ሕዝብ ነን። ምን ያህል እየተጠቀምን ነው? የሚለው ሌላ ጉዳይ ሆኖ ከእነዚህ ሀብቶች ውስጥ አንዱ የግዕዝ ቋንቋችንና ፊደል ነው። ይህ ፊደላችን ቀደም ባለው ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት በትምህርት ቤቶች፤ በብሔራዊ ፈተናም ጭምር ይሰጥ ነበር። ምናልባት የዛሬውን ሁኔታ የምናየው ቢሆንም ቀደም ባለው ጊዜ የነበረበት ግን በተሻለ ደረጃ የምናውቀው ነው፤ ያም ሆኖ የእዚህ ቋንቋና ፊደል ዕድገቱ ያን ያህል ነው? ከእዚህ ባለፈ ቀደም ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ሠራተኞች በተለይም የቢሮ ፀሃፊዎች አማርኛን ቋንቋ በጽሕፈት መኪና ላይ ሲጽፉ የእንግሊዝኛው ገበታ እንዳስቸገራቸው ተመለከትሁ፤ ይህ በውስጤ ጥያቄ አስነሳ " ይላሉ።

በተጨማሪም የሚጽፉት የአማርኛ ጽሑፍም ትክክለኛው አይደለም፤ በይመስላልና በይሆናል የሚጻፍ ስለሆነ ችግሩ የጐላ መሆኑን አየሁ። ቋንቋውም መፃፍ ያለበት በደንበኛው የእራሱ ፊደል እንጂ በሚቀጠል ፊደል መሆን የለበትም ስልም አሰብኩ። ስለዚህ አሜሪካ ሄጄ ትምህርቴን መማር ስጀምር እ.ኤ አ በ1975ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ኮምፒዩተርን አየሁ። ኋላም ለምርምሬ የምጠቀመው ይሄው መሣሪያ ሆነ። ከእዚያ መሣሪያው ለወደፊቱ ብዙ ጥቅም እንዳለው ሳይ ሃሳብ ማውጣትና ማውረድ ጀመርኩ ይላሉ። በእዚህም እኔ የምሠራው ነገር አዲስ በመሆኑ እራሴ ዘዴውን መፍጠር ነበረብኝ፤ ሆኖም ግን በግዴታም ቢሆን በእራሴ ጥረትና ተነሳሽነት ሥራው ሊሳካ ችሏል ይላሉ።

ዶክተር አበራ በእንስሳት ሕክምና ሙያቸውም በተለይ በኢምዩን ደፊሸንሲ Immune Deficiency Patent ይታወቃሉ። ባደረጉት ምርምርና ውጤት ኢምዩን ደፊሸንሲን በማስወገድ በየዓመቱ ሲጠፉ የነበሩትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳቶችን ሕይወት ማትረፍ ችለዋል።

ከሰው ልጅ እናቶችና ከአንዳንድ የጦጣና ውሻ ዝርያዎች በስተቀር የሌሎች እንስሳት ማህጸኖች ኢምዩኖግሎቡሊን (Immunoglobulin) የሚባለውን የበሽታ መከላከያ ፕሮቲን ለጽንሶቻቸው በእርግዝና ጊዜ አያስተላልፉም። አጥቢ እንስሳት በእርግዝና ጊዜ በአካባቢው ለሚገኙት በሽታዎች መከላከያዎች በእንገርነት ያከማቹላቸውና አራሶቻቸው እንደተወለዱ ጡት ሲጠቡ የበሽታ መከላከያዎቹ ፕሮቲኖች ሳይለወጡ ከአንጀት ወደ ደም በመግባት ለጥቂት ሳምንታት ከበሽታዎች ይከላከሉላቸዋል።

ጥጆቹ እንገሩን ሳያገኙ ከቆዩ ግን ወደ ደም መግባታቸውና መከላከያነታቸው ቀርቶ እንደ ተራ ፕሮቲን ምግብ ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ጥጆች ሲወለዱ የኤድስ ቫይረስ የበሽታ መከላከያቸውን እንደጨረሰ ሰው ምንም መከላከያ ስለሌላቸውና አካባቢው ያሉትን የበሽታ ጀርሞች እየቀማመሱ በተለያዩ በሽታዎች የእራሳቸውን መከላከያ መሥራት እስከሚጀምሩ ድረስ እየተጠቁ አብዛኛዎቹ ይታመማሉ፣ ወደ አሥር ከመቶም ይሞታሉ። ታክመው የሚድኑትም አይጠረቁም። በኮሎራዶ እስቴት ዩኒቨርሲቲ (Colorado State University) የዶ/ር አበራ የድህረ ዶክትራል ምርምር ይህን ችግር ለመቋቋም መፍትሔ ሆኖ መጣ። በዶ/ር አበራ ሞላ ግኝት እስከ ለዘመናት ጠንቅ ሆኖ የቆየውን መድኃኒት የሌለውን የእንስሳትን ኤድስ ዓይነት ሁኔታ (Failure of Passive Transfer / FTP) ሃምሳ በመቶ መቆጣጠርና ማስወገድ ተችሏል።

የዶክተሩ ዘዴ ለተለያዩ ለማዳና የዱር እንስሳት ጥቅም ላይ እየዋለ እስከ ዛሬ ቀጥሏል። ዩናይትድ እስቴትስ ውስጥ በየዓመቱ ከሚወለዱት 40 ሚሊዮን ጥጃዎች 4 ሚሊዮን የሚሆኑት በመድኅን ማነስ ሊሞቱ ይችሉ የነበሩት በዶክተሩ ግኝት ባለፉት አርባ ዓመታት ሊተርፉ ችለዋል። በተጨማሪም ሰላሳ በመቶ ጥጃዎች ሕክምና እንዲያገኙ ሆኗል።

እኛም በዚህ ለሀገርና ሕዝብ በሙያቸው የሠሩና ታላቅ ዐሻራ ማኖር የቻሉ ኢትዮጵያውያን በሚመሰገኑበት አምዳችን የግዕዝ የኮምፒዩተር ፅሁፍ አባትና የእንስሳት ሐኪም የሆኑትን ዶክተር አበራ ሞላን አመሰገንን። ሰላም !

# ስፖርት



# ክልሉ ተጨማሪ ክለቦችንና ፕሮጀክቶችን ለማቋቋም ጥረት እያደረገ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ስፖርት በሀገሪቱ በሚገኙ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ስር በተዋቀሩ ፌዴሬሽኖች አማካኝነት ከብሄራዊው ፌዴሬሽን በሚወጡት ሕግና ደንቦች ላይ ተመስርቶ ይመራል። ክልላዊ ፌዴሬሽኖች ደግሞ የሀገሪቱን የእግር ኳስ እንቅስቃሴ ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን በየፊናቸው ያከናውናሉ። በቅርብ ጊዜ ከተቋቋሙትና ጥሩ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ከሚገኙት ክልላዊ የእግር ከኳስ ፌዴሬሽኖች መካከል የሲዳማ ክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽን ይጠቀሳል። ክልሉ በበኩሉ ያለውን እምቅ የእግር ኳስ አቅም አሟጦ ለመጠቀም በጥረት ላይ ይገኛል።

በሲዳማ ክልል በተለይም ሃዋሳ ከተማና አካባቢዋ ከፍተኛ የእግር ኳስ እምቅ ተሰጥኦዎች የሚገኙበትና በርካታ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን መወከል የቻሉ ተጫዋቾች የወጡበት ነው። ከተመሠረተ አራት ዓመት ያስቆጠረው ፌዴሬሽኑ የክልሉን እግር ኳስ ለማሳደግ በዞኖችና በወረዳዎች እንደየደረጃው አስተዳደሮችን በማዋቀር የተሻለ እንቅስቃሴን በማድረግ ላይ ነው። ፌዴሬሽኑ በቅርብ ጊዜ የተመሠረተ ቢሆንም ባሳየው የላቀ የሥራ አፈጻጸም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሁሉም ፌዴሬሽኖች ቀዳሚ ነው። የተለያዩ የውስጥ ውድድሮችን ማካሄድ እና ሀገራዊ ውድድሮችን ተቀብሎ በማስተናገድ ረገድም ትልቅ ሚናን በመወጣት ላይ ይገኛል።

በክልሉ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ሶስት የታዳጊ እግር ኳስ ፕሮጀክቶች ቢኖሩም በቂ የሚባል ባለመሆኑ ቁጥሩን ከፍ ለማድረግ ታቅዶ እየተሠራ ነው። ይህም



የሲዳማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ተፈራ፤

ከፍተኛ ፋይናንስን የሚጠይቅ በመሆኑ ለዛ እንዲረዳ ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑንም ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

በክልሉ የሚገኙትን ሁለት በፕሪምየር ሊግ በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ በማድረግ ላይ የሚገኙትን ክለቦች (ሃዋሳ ከተማ እና ሲዳማ ቡና እግር ኳስ ክለቦችን) ከማጠናከርና ከማገዝ ባለፈ ተጨማሪ ክልሉን የሚወክሉ ክለቦችን ለመፍጠር ሂደቶችን ጀምሯል።

የክልሉ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ተፈራ፣ ፌዴሬሽኑ አማተር ባለሙያዎችን በመያዝ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ያስረዳሉ። ፕሮጀክቶችንም ለማቋቋም ዝግጅት እየተደረገ ነው። የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል፣ የመሣሪያ እንዲሁም ሜዳ ለማሟላት ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም እና ስፖርት ኮሚሽኑ የድጋፍ ማመልከቻ ደብዳቤ በማስገባት ተጠይቋል። ለአሠልጣኞች እና ሠልጣኞች የሚያስፈልገውን የትጥቅና ሌሎች ነገሮች ለማሟላት የሚያስችል ዝግጅትም እየተደረገ ነው። ፕሮጀክቶቹን ይዘው ማሠልጠን የሚችሉና በሙያቸው ብቁ አሠልጣኖችን በማሠልጠን የቅድመ ዝግጅት ሥራም ተከናውኗል።

የክለቦችን ቁጥር ለመጨመር በሚደረገው ጥረት ሁለት ክለቦች ወደ አንደኛ ሊግ አድገው ውድድራቸውን ማድረግ ቢችሉም አንዱ በበጀት እጥረት በመቅረቱ ቀጣይ የሚወዳደሩትን ክለቦች ለመያዝ ከስፖርት ኮሚሽኑ ጋር እየተነጋገሩ መሆኑን ኃላፊው ጠቁመዋል። የበጀት እጥረቱን በመቅረፍ ዘላቂነት ያላቸውን ክለቦች ለመፍጠር ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ክለቦች የሚደገፉበት ሁኔታም ይፈጠራል።

ክለቦቹ ውድድር ሲያካሄዱ ወረዳን፣ ዞንን እና ከተማን በመወከል የሚመጡ በመሆኑ ከክለቦቹ ጋር የሚተሳሰሩበትን እና መደገፍ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የሚሳተፉ ተጨማሪ ጠንካራ ክለቦችን ለማፍራት ታቅዶ እየተሠራም ይገኛል።

በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከፍተኛ ድምቀትን እየፈጠሩ የሚገኙት ከሃዋሳና ዙርያዋ የወጡ እግር ኳስ ተጫዋቾች በርካታ ሲሆኑ ይሄን አጠናክሮ ለመቀጠል ፕሪምየር ሊጉን ጨምሮ በከተማዋ የሚደረጉ ውድድሮች የክልሉን የእግር ኳስ እምቅ አቅምን አውጥቶ ለመጠቀም እድል እንደሚፈጥር ኃላፊው ይጠቁማሉ።

የፕሮጀክቶችን እና ቡድኖችን ቁጥር ለመጨመር በሚደረገው ጥረት የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ ከባህልና ቱሪዝም እንዲሁም ከክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ጋር በመነጋገር በጀት ለማስመደብና የተለያዩ የውስጥ ገቢዎችን በመፍጠር እግር ኳሱ እንዲጠናከርም ይሠራል።

ከወረዳዎች ዞኖችና ከተሞች የተውጣጡ 10 ቡድኖች እተካሄደ በሚገኘው የክልሉ የክለቦች ቻምፒዮና እየተፎካከሩ ሲሆን የሚያሸንፉ ክለቦች ክልሉን ወክለው በክልል ክለቦች ቻምፒዮና፣ ማሸነፍ ከቻሉ ደግሞ በኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ ክልሉን ወክለው ይወዳደራሉ። በዚህም መሠረት አንደኛና ሁለተኛ የወጡ ክለቦች ክልሉን በመወከል የክልል ክለቦች ቻምፒዮና ላይ የሚሳተፉ ይሆናል። ውድድሩ ክልሉን የሚወክሉ ክለቦችን ከመፍጠር ባሻገር ታዳጊ ተጫዋቾች እራሳቸውን እንዲያሳዩና ልምድ ቀስመው ትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ መንገድ እንደሚከፍት ተጠቅሷል።

እግር ኳሱን ለማሳደግ ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል የማዘውተርያ ሥፍራ (ሜዳ) በመሆኑ በሃዋሳ ከተማ የሚገኙ ሜዳዎችን የማስተካከልና ያልታጠሩትን የማሳጠር እና በከተማዋ ውስጥ የሚገኙትን ሜዳዎችን በሙሉ በክልሉ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስር እንዲተዳደሩ የማድረግ ሥራዎች ለማከናወንም ታቅዷል።